# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

84ኛ ዓመት ቁጥር 022 መስከረም 22 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












ምስል፡- ከማህበራዊ ድረገጽ

# የሰላም ስብራቱ ወጌሻ

**ተስፋ ፈሩ**

በሀገራዊ ምክክር ዙሪያ ጥናት ያደረጉት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህሩ እና የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ፓርቲ ምክትል መሪ አርክቴክት ዮሐንስ መኮንን እንደሚገልጹት፤ ብሔራዊ ምክክር በሥርዓተ መንግሥት እና በሀገራዊ ተቋማት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት እንደገና መገንቢያ መንገድ ነው። በግጭት የተለያዩ ማኅበረሰቦችን እንደገና ማሰባሰቢያ አጀንዳ እና አዲስ ማኅበራዊ ውል ማሠሪያ ገመድም ነው።

ሀገራት ውስጣዊ መሰንጠቅ እና የመበተን አደጋ ሲጋረጥባቸው የሚሻገሩበት ድልድይ፤ አለመረጋጋት እና የግጭት አዙሪት ሲንጣቸውም ከውድቀት መውጫ ምርኩዛቸው ነው። ሥርዓተ መንግሥት መገንባት ላልቻሉ ሀገራት ደግሞ ሕዝባቸውን በጋራ የታሪክ መሠረት፣ በዛሬ እኩልነትና በነገ ተስፋ ማሰባሰቢያ ነጋሪት ሆኖ ያገለግላል።

የሥርዓተ መንግሥት ግንባታቸውን በቅጡ ያልጨረሱ፣ በግጭት እና በኢኮኖሚ ውድቀት አዙሪት ውስጥ ለሚማቅቁ ኢትዮጵያን ለመሰሉ ሀገሮች ውይይቶቹ የሚመልሷቸው በርካታ ዝርዝር ጉዳዮች ስለሚኖሩ ሀገራዊ ውይይት (National Dialogue) ጥቅሙ ብዙ ነው ባይ ናቸው።

ለመሆኑ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር ለሀገረ መንግሥት ግንባታ እንዲውል ምን አይነት አስቻይ ሁኔታዎች አሉ ?

ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ "መግባባት ፖለቲካዊ ዕኩልነት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን" በሚል ርዕስ በ2015 ዓ.ም አሻሽለው ባሳተሙት መጽሐፋቸው፤ ለሀገራችንና ለወገኖቻችን የሚበጅ ሃሳብ ማመንጨትና በሥራ ላይ ማዋል የሚቻለው በመነጋገር ነው ይላሉ።

ትልቅነት የሚመጣው በሃሳብ የምንለያይ ወገኖች በበጎ

የሰላም ስብራቱ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ለትውልድ መልካም እሴትን ያሻገሩ አረጋውያንን ማክበርና ፍቅር መስጠት ሀገር ወዳድነት ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ለትውልድ መልካም እሴትን ያሻገሩ አረጋውያንን ማክበርና ፍቅር መስጠት ሀገር ወዳድነት ነው ሲል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአረጋውያንና ቤተሰብ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ሮበሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለሀገር በየተሠማሩበት ሃላፊነት ሃላፊነትን በመወጣት ብዙ ውለታ የሠሩ ፤ ለትውልድ መልካም እሴትን ያሻገሩ

ለትውልድ መልካም ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ምክር ቤቱ የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት ደንብን አጸደቀ

ገጽ 2

# የኢሬቻው ድምቀት

**መስከረም ሰይፉ**



የበዓላት ወቅት ሲደርስ የበዓሉን ድባብ ከሚፈጥሩ ነገሮች መካከል የባህል አልባሳት ተጠቃሽ ናቸው። ድሮ ድሮ የባህል አልባሳት በብዙዎች ዘንድ የማይመቹ ተደርገው የሚታሰቡ የነበረ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የፋሽን ኢንዱስትሪው የባህል አልባሳትን በተለያየ ስልት እየሸመነ ሰዎች በዓላትን ሳይጠብቁ ጭምር እንደየምርጫቸው በባህላቸው እንዲያጌጡ እያደረገ ይገኛል።

በተለያዩ ስልቶች የተዋቡ የባህል አልባሳት ከሚስተዋሉባቸው በዓሎች አንዱ ኢሬቻ ሲሆን በዚህ በዓል ላይ ከህጻናት ጀምሮ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች

የኢሬቻው... ወደ ገጽ 8 ዞሯል






አቶ ግርማ ቱፋ

## የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ የማስፋፊያ ግንባታ በ300 ሚሊዮን ዶላር ይከናወናል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዳማ፡- የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሁለተኛ ምዕራፍ የማስፋፊያ ግንባታ በ300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማከናወን ዝግጅት እያጠናቀቀ መሆኑን ገለጸ።

የኢንዱስትሪ ፓርኩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ግርማ ቱፋ ለኢዜአ እንደገለፁት፤ በመጀመሪያው ዙር የተከናወነው የኢንዱስትሪ ፓርኩ አካል በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ በባለሀብቶች ተይዟል።

ዘንድሮ ግንባታው የሚጀመረው ሁለተኛው ምዕራፍ የኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ ከ120 ሄክታር በላይ መሬት ላይ የሚያርፍ መሆኑንም ተናግረዋል።

"የፓርኩ ግንባታ በ300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚከናወን ነው" ያሉት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ ለዚህም ከቻይና ሁናን ግዛት የመጡ ባለሀብቶች ግንባታውን ለመጀመር መግባባት ላይ ተደርሷል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት ከከተማ አስተዳደሩ ጋር ወሰን የማስከበር ሥራ እየተጠናቀቀ መሆኑን ጠቅሰው፤ ግንባታውን ለመጀመር የዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

የፓርኩ ግንባታ ሲጠናቀቅ ትላልቅ ማሽነሪዎች የሚመረቱበትና ሀገሪቷ ለዚህ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ከማስቀረት ባለፈ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑንም ተናግረዋል።

የሁለተኛ ምዕራፍ የፓርኩ ግንባታ ሲጠናቀቅ ከ25 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑንም አመልክተዋል።

በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ በመጀመሪያ ምዕራፍ የተገነቡ ሼዶች ሙሉ በሙሉ በባለሀብቶች የተያዙ ሲሆን ከ 13ቱ ባለሀብቶች ውስጥ 11 ባለሀብቶች በምርት ላይ እንደሚገኙ ተመላክቷል።

ፓርኩ ባለፈው ዓመት 2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ግምት ያለው ተኪ ምርቶችን በማምረት ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረቡ የተገለጸ ሲሆን፤ በዘንድሮው ዓመት ለውጭ ገበያ ከሚያመርተው በተጨማሪ 3 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ ተኪ ምርቶችን ለማምረትና ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል።

# ምክር ቤቱ የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎት ደንብን አጸደቀ

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡ -የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢሚግሬሽን እና የዜግነት አገልግሎትን የተመለከቱ ሁለት ደንቦችን አጸደቀ። የሚኒስትሮች ምክር ቤት በትናትናው ዕለት ባካሄደው 39ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ39ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ከሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ደንብ እና የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ሠራተኞች ደንብ ተጠቃሽ ናቸው።

ደንቡ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር እና ሃላፊነት ለመወጣት፤ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለደንበኞች ለመስጠት እንዲሁም ከፓስፖርት የቆይታ ጊዜ ጋር በተያያዘ ያሉ ጥቄዎችን መፍታት እንዲችል የተዘጋጀ መሆኑ ተገልጿል።

እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ የጀመረውን ሪፎርም ውጤታማ ለማድረግና በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበር ለማስቻል የአገልግሎቱን ልዩ ባህሪይ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን ፤ምክር ቤቱም በረቂቅ ደንቦቹ ተወያይቶ በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረጉ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ ብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን 2017-2020 የገቢ ስትራቴጂ ላይ የተወያየ ሲሆን ስትራቴጂው የታክስ ሥርዓቱን ለማዘመን እና ለግል ኢንቨስትመንቱ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የታለመ መሆኑም ተነስቷል።

ይህም የታክስ ፖሊሲዎችን እና አስተዳደራዊ ሪፎርሞችን እንዲሁም ማሻሻያዎችን ለመተግበር የሚያስችል እና ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ተደርጎ የቀረበ ነው። ምክር ቤቱም በስትራቴጂው ላይ በዝርዝር በመወያየት አጽድቆታል።

እንዲሁም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከማልታ ሪፐብሊክ መንግሥት እና ከቻድ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተፈራረማቸውን የአየር አገልግሎት ስምምነቶችን ለማጽደቅ የቀረቡ ሁለት ረቂቅ አዋጆች ላይ ምክር ቤቱ ተወያይቷል።

ስምምነቶቹ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ማንኛውም የማልታ ከተማ እና ወደ ኢንጃሚና ከተማ በ3ኛና 4ኛ ትራፊክ መብት የመንገደኛ እና የጭነት የበረራ ምልልስ ለማድረግ፣ ተወካይ አየር መንገዶችን በሽርክና ለማሠራት፣ በ5ኛ ትራፊክ መብት ወደ ተመረጡ መዳረሻዎች በረራ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ተነስቷል።

ረቂቅ አዋጆቹ ሀገሪቱ ከሁለቱ ሀገራት ጋር ያላትን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር፣ ለንግድና ኢንቨስትመንት፣ ለወጪ ንግድ፣ ለቱሪዝም፣ ለሥራ እድል ፈጠራ እና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ትልቅ አስተዋጽኦ ያላቸው ስምምነቶች በመሆናቸው ምክር ቤቱ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፉ ውሳኔ ሰጥቷል።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ የዓለም አቀፍ ምልክቶችን ከሚመለከተው የማድሪድ ስምምነት ጋር የተዛመደውን ፕሮቶኮል ለማጽደቅ በወጣ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል።

በውይይቱም ፕሮቶኮሉ የንግድ እና የአገልግሎት ምልክቶች በሀገር ውስጥ ሕግ ከሚደረግላቸው ጥበቃ አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥበቃ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ከመሆኑም በተጨማሪ ምርቶች እና አገልግሎቶች ያላግባብ ለሌሎች ጥቅም እንዳይውሉ በቂ ጥበቃ የሚደረግበትን ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ በውይይቱ ላይ ተነስቷል።

እንዲሁም ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶችና አገልግሎቶች እንዲኖሩና የሀብት ምንጭ እንዲሆኑ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ምክር ቤቱ በፕሮቶኮሉ ላይ ከተወያየ በኋላ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ የፓሪስ ኢንዱስትሪያዊ ንብረት ኮንቬንሽንን ለማጽደቅ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል።

በውይይቱም በአባል ሀገራት መካከል ሕብረት በመፍጠር የኢንዱስትሪ ንብረትን ለመጠበቅ፣ የፈጠራ ባለቤትነት፣ የኢንዱስትሪ ንድፎች፣ የንግድና የአገልግሎት ምልክቶች፣ የንግድ ስሞች፣ የምርቶች ምንጭ አመልካች ምልክቶች ለመጠበቅ የሚያችል መሆኑ ተነስቷል።

በመሆኑም የኮንቬንሽኑ መጽደቅ ሀገሪቱ ለምታደርገው የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ጥያቄ ድጋፍ የሚሆን ሲሆን ከአባል ሀገራቱ ለሚነሱ የኢንዱስትሪያዊ ንብረት ጥበቃን ለሚመለከቱ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ ለመስጠት የሚያስችል መሆኑ ተጠቁሟል።

በዚህም ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

# የደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎትን ለማሳደግ የፋይናንስ ሥርዓቱን የማጠናከር ተግባር ይከናወናል

**ሶሎሞን በየነ**



ፎቶ፡ ሀዱሽ አብርሃ

አሸናፊ ታዘበው(ዶ/ር)

አርባ ምንጭ፡- የደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎትን በሚፈለገው ልክ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግና ይበልጥ ለማሳደግ የፋይናስ ሥርዓቱን የማጠናከር ሥራ በልዩ ትኩረት እንደሚሠራ የኢትዮጵያ ደም እና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ።

12ኛው የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንኮች ዓመታዊ ጉባዔ “ዘላቂ ፋይናንስ - ለጠንካራ ደምና ሕብረ ህዋስ አገልገሎት” በሚል መሪ ሃሳብ በአርባ ምንጭ ከተማ ተካሂዷል።

በጉባዔው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ደም እና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አሸናፊ ታዘበው (ዶ/ር) እንዳሉት፤ የደምና ሕብረ ህዋስ አገልግሎቱ ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት በሚመደብ መደበኛ በጀት እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በሚመደብ በጀት የሚሰጥ ነው።

ሆኖም ህብረተሰቡ በሚፈልገው ልክ አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም ለመሰብሰብና ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ከታቀደው ደምና ህብረ ሕዋስ አንጻር በጀቱ በቂ ነው ተብሎ አይታሰብም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በመሆኑም የደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎትን በሚፈለገው ልክ ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግና ይበልጥ ለማሳደግ የፋይናንስ ሥርዓቱን የማጠናከር ሥራ በልዩ ትኩረት ይሠራል ብለዋል።

ዶክተር አሸናፊ የፋይናንስ ሥርዓቱን ለማጠናከር በተግባር ወደ ሥራ መገባቱን ገልጸው፤ የደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎቱ የሚጠይቀውን ወጪ (የኮስት አናሊስስ) በመሥራት “ወጪው እንዴት ይተካል” ከሚለው የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ ጭምር ለሚመለከተው አካል በዚህ ዓመት ውስጥ በማቅረብ የማጸደቅ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

እርሳቸውም፤ ደም ከተሰበሰበ በኋላ ሂደቶችን አልፎ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እስኪደርስ ድረስ ባለው ሂደት ያለውን ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል ዘዴዎችን በመንደፍ ለሚመለከተው አካል ምክረ ሃሳቡን የምናቀርብ ይሆናል ብለዋል።

የአገልግሎቱን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በስፋት ለአጋርና ለሚመለከታቸው አካላት የማስተዋወቅና የማስገንዘብ ሥራ በስፋት እንደሚከናወን አመላክተው፤ በዚህም ከአጋርና ከሚመለከታቸው አካላት ሊገኙ የሚችሉ የፋይናንስ ምንጮችን ወይም እድሎችን ከፍ የማድረግ ሥራ እንደሚከናወን ተናግረዋል።

ዶክተር አሸናፊ፤ ጤና ሚኒስቴር እንዲሁም የክልል ጤና ቢሮዎች ለአገልግሎቱ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው የበጀት፣ የሰው ኃይል አመዳደብና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በትኩረት እንዲሠሩ አሳስበው፤ በ2017 ዓ.ም የፋይናንስ አቅምን ከማጠናከር ባሻገር የአገልገሎት ተደራሽነት፣ ጥራትና ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለመጨመር ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በበጀት ዓመቱ በመላ ሀገሪቱ ያሉትን 50 ደም ባንኮች ወደ 54 ለማሳደግ እየተሠራ እንደሆነ ጠቁመው፤ ቁጥራቸውን ከማሳደግ ባለፈ ደም ባንኮቹ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እንዲሰጡ በትኩረት ይሠራልም ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪም በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰነውን የዐይን ባንክ አገልግሎት ቢያንስ ከመዲናዋ ባሻገር በሌላ አንድ ክልል አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተመሳሳይ ተባብረን እየሠራን እንገኛለን ብለዋል።

በጉባዔው የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የሕዝብ እንደራሴዎች እና የክልሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎች፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ተጽዕኖ ፈጣሪነትና ተሰሚነት ያላቸው የሃይማኖት አባቶች፣ አርቲስቶች እንዲሁም የገዢውና የተፎካካሪ ፓርቲዎች አባላት እየተሳተፉ ይገኛል።

# ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ከሚኖሩ የዳያስፖራ ማህበራት የተሰበሰበ አጀንዳ ተረከበ

## - በአፋር ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክም አካሂዷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኢትዮጵያ ከሚኖሩ የዳያስፖራ ማህበራት የተሰበሰበ አጀንዳ እና በአርቲስት ዘለቀ ገሰሰና በሙያ አጋሮቹ “እንመካከር” በሚል ርዕስ የተሠራውን የሙዚቃ ክሊፕ በትናንትናው ዕለት ተረከበ። ኮሚሽኑ በአፋር ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱንም በትናንትናው እለት አስጀምሯል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በሀገሪቱ የማያግባቡ ጉዳዮችን በምክክር እና በሠለጠነ መንገድ ለመፍታት እየሠራ ይገኛል።

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የሀገራዊ ምክክሩ ቁልፍ ተሳታፊዎች በማድረግ እየሠራ ይገኛል ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ ቀደም ሲል በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአውሮፓ፣ በካናዳ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በሌሎች ሀገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ስለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ዓላማ ከ10 በላይ የበበይነ መረብ ውይይት ማደረጉን አውስተዋል።

በኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከተኛል የሚል የማንም ጥያቄ አይቀርም ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሀገራዊ ፋይዳ አላቸው የሚሏቸውን ጥያቄዎች በአጀንዳ መልክ ቀርጸው በጋራም ሆነ በተናጥል ለኮሚሽኑ መላክ ይችላሉ ነው ያሉት።

በውጭ ሀገር ያሉ ኢትዮጵያውያን በተደራጀ መልኩ ጥያቄያቸውን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ኮሚሽኑ ወደ ተወሰኑ የውጭ ሀገራት በአካል በመሄድ ስለሀገራዊ ምክክሩ ጽንሰ ሃሳብ፣ እየተሠሩ ስላሉ ሥራዎች እና የወደፊት አካሄዱን በተመለከተ በሀገራቱ ከሚገኙት ኢትዮጵያውያን ጋር ውይይት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

በውይይቱም ለሚነሱ ጥያቄዎች፣ ብዥታ ፈጥረው እስካሁን በቆዩ ጉዳዮች እና ሀገራዊ ምክክርን በተመለከተ ተገቢውን ገለጻ እናደርጋለን ሲሉ አስረድተዋል።

ለሀገራዊ ምክክሩ ግብዓት የሚሆኑ አጀንዳዎች በተለያዩ ክልሎች ሲሰበሰብ እንደነበር አስታውሰው፤ በትናንትናው ዕለት ደግሞ በኢትዮጵያ ከሚኖሩ የዳያስፖራ ማህበራት የተሰበሰበ አጀንዳ መረከባቸውን ገልጸዋል።

ከወረዳ ጀምሮ የማያግባቡ ጉዳዮች በማዕከል ደረጃ ወደ ኮሚሽኑ እየቀረቡ ያሉበት ምዕራፍ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይ ጊዜ ግለሰቦች አጀንዳቸውን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እና በቀጥታ ወደ ኮሚሽኑ የሚያቀርቡበት እንዲሁም ከወረዳ እስከ ማዕከል እና በፌዴራል ደረጃ አጀንዳቸውን ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ ብለዋል።


መስፍን አርዓያ (ፕ/ር)

ኮሚሽኑ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚያቀርቡትን አጀንዳ በማንኛውም ጊዜ ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን አረጋግጠዋል።

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሀገራዊ ምክክሩ እየሠራው ስላለው ሥራ እና ስለወደፊት አካሄዱ ግንዛቤ ሊኖራቸው እንደሚገባ እና ንቁ ተሳትፎ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ዲያስፖራ ማህበር ፕሬዚዳንት አርቲስት ዘለቀ ገሰሰ እንመካከር በሚል ርዕስ አዘጋጅቶ ለምክክር ኮሚሽኑ ከዚህ በፊት በድምጽ ቅጂ ብቻ ያበረከተውን የሙዚቃ ክሊፕ ያስረከበ ሲሆን፤ ለአርቲስት ዘለቀና የሙያ አጋሮቹ ምስጋና አቅርበዋል።

ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ከዚህ ትምህርት በመውሰድ በሚሠሩበት የሙያ መስክ ሀገርና ሕዝብን ሊያገለግሉ እንደሚገባም ተናግረዋል።

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚገኙ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ስለሰላም መሥራት ዋና ኃላፊነታቸው ሊሆን እንደሚገባም ጨምረው ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ዲያስፖራ ማህበር ፕሬዚዳንት አርቲስት ዘለቀ ገሰሰ በበኩሉ፤ ኪነጥበብን በመጠቀም በሀገሪቱ ያሉትን ግጭቶችና አለመግባባቶች በመፍታት ለሰላም፣ ለፍቅር እና ለአንድነት መሥራት ይገባል ብሏል። በዚህም ከሙያ አጋሮቹ ጋር በመሆን በህብረተሰቡ መካከል ሰላም፣ ፍቅር፣ መግባባት እና ሀገራዊ አንድነትን የሚሰብክ ሙዚቃ ሠርቼ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር አስረክቤያለሁ ሲል ተናግሯል።

ኪነጥበብ የህብረተሰብ መስታወት በመሆኑ በቀጣይም ሌሎች የኪነጥበብ ባለሙያዎች በዚህ ሥራ እንዲሳተፉ ጥሪ እናቀርባለን ሲል አስታውቋል።

በተያያዘም የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በአፋር ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክን ትናንት አስጀምሯል።

የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ ማስጀመሪያ መርሃግብር ላይ ንግግር ያደረጉት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር አምባሳደር አይሮሪት መሐመድ (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ ኮሚሽኑ ትናንት ተጀምሮ ለቀጣዮቹ ስድስት ቀናት በሚቆየው አጀንዳ የማሰባሰብ ተግባር ተሳታፊዎች ከሚያደርጉት ንግግር እና ምክክር ሀገራዊ መግባባት ላይ ልንደርስባቸው ያስፈልጋል ብለው የሚያምኑባቸውን የዳበሩ አጀንዳዎች ይሰበስባል።

የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እና ባለድርሻ አካላትን በመወከል የሂደቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ተወካዮች የሚያፀባርቋቸው ሃሳቦች በአፋር ክልል ብሎም በሀገር ደረጃ መግባባትን ለማስፈን ቁልፍ ሚና እንደሚኖራቸው የጠቆሙት ኮሚሽነሯ፤ ተሳታፊዎች በሃላፊነት ስሜት የአጀንዳ ሃሳቦቻቸውን እንዲያቀርቡ ጠይቀዋል።

አክለውም፤ የሀገራችን ኢትዮጵያ ችግሮች ዘርፈ ብዙ መሆናቸው የሚታወቅ ቢሆንም እኛው ኢትዮጵያውያን በሰከነ መንፈስ የሃሳብ ልዩነቶቻችን ላይ ለመነጋገር መፍቀዳችን ለችግሮቻችን ለዘለቄታው የሚበጁ መፍትሔዎችን ለማስቀመጥ ያግዘናል፤ የጋራ ቤት ለመገንባትም ያስችለናል ብለዋል።

አካታችነት ከኮሚሽኑ መርሆዎች አንዱ መሆኑን አመላክተው፤ ከተሳታፊዎቹ ውስጥ ሴቶች 30%፣ አካል ጉዳተኞች 10%፣ ወጣቶች 20% እንዲሆኑ የኮሚሽኑ የአሠራር ሥነ ዘዴ በሚያዘው መሠረት ተሳታፊዎች በወካዮቻቻቸው አማካይነት ተመርጠው የምክክር ሂደቱ መጀመሩን ነው ኮሚሽነሯ የተናገሩት።

በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደቱ በአፋር ክልል ከሚገኙ ከ49 ወረዳዎች የተመረጡ ከ800 በላይ የሕብረተሰብ ክፍል ወኪሎች እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ ከ700 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች፣ የመንግሥት ተወካዮች፣ የተለያዩ ተቋማትና ማህበራት ተወካዮች እንዲሁም ታዋቂ ግለሰቦች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወል አርባ በተገኙበት የተጀመረው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት በሀገር ሽማግሌዎች ቡራኬ እና በሃይማኖት አባቶች ፀሎት የተከፈተ ሲሆን፣ የሴቶች እና ወጣቶች ተወካዮችም መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኮሚሽኑ እስካሁን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በሐረሪ፣ በሲዳማ እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች የአጀንዳ ማሰባሰብ መድረኮችን አካሂዷል።

# የቱሪዝም መዳረሻዎች ለቱሪስቶች ምቹ ሁኔታ እየፈጠሩ ነው

**ማርቆስ በሳይ**

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለቱሪስቶች ምቹ በማድረግ በኩል አበረታች ሥራዎች መሠራታቸውን የኦሮሚያ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ከፍያለው ተፈራ ገለጹ።

የኢሬቻ በዓልን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው 4ኛው የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንትና ኤግዚቢሽን ትናንት በአዲስ አበባ በይፋ ተከፍቷል።

የኦሮሚያ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ከፍያለው ተፈራ በመድረኩ ተገኝተው እንደገለጹት፤ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት የቱሪዝም መስህብ ቦታዎችን በማልማት ለቱሪስቶች ዝግጁ ማድረግ ተችሏል።

ኦሮሚያ የተፈጥሮ ሀብትና ባህላዊ እሴቶችን የተሸለመች ክልል ናት ያሉት ኃላፊው፣ የለውጡ መንግሥት በሁሉን አቀፍ ሪፎርሙ ላይ የቱሪዝሙ ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲለማ ታቅዶ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የክልሉ መንግሥት 28 ፓርኮችና ኢኮ ቱሪዝሞችን በመለየት ለምተው ለቱሪዝሙ ግብዓት እንዲሆኑ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፣ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመቀናጀት የቱሪዝም መስህብ ቦታዎችን በማልማት ለቱሪስቶች ዝግጁ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

በቱሪዝሙ ዘርፍ ያለው ሀብት በርካታ በመሆኑ በአግባቡ በማልማት ለወጣቶች የሥራ እድል መፍጠር እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፣ ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማሳካት ሁሉም የድርሻውን ከተወጣ የዜጎችን ሕይወት መቀየር እንደሚቻል ተናግረዋል።



የቱሪዝሙ ኢንዱስትሪ ከሰላም ጋር ያለው ትስስር ትልቅ ነው ያሉት አቶ ከፍያለው፣ ከቱሪዝም ዘርፉ ሀብት ማመንጨት የሚቻለው ሰላምና መረጋጋት ሲኖር ብቻ ነው ብለዋል።

ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ጠቅሰው፣ ሰላምን ማረጋገጥ ከተቻለ የዘርፉን ሀብት በማልማት የዜጎችን ሕይወት በአጭር ጊዜ መለወጥ እንደሚቻል ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ በበኩላቸው፤ ቱሪዝም ድንበር የለሽ በመሆኑ መላውን ሕዝብ አግባብቶ የሚያሳትፍ ዘርፍ ነው ብለዋል።

በቱሪዝም ሳምንቱ የተለያዩ የሆቴል፣ የቱሪዝም፣ የጉዞና አስጎብኚ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበት የቱሪዝም ኤግዚቢሽን ተዘጋጅቷል ያሉት ኮሚሽነር ሌሊሴ፣ በኤግዚቢሽኑ የሀገር ውስጥ አቅራቢዎችን ጨምሮ ከኬንያ፤ ሩዋንዳ፤ ኡጋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ሴራሊዮን፣ ኔፓልና የተለያዩ ሀገራት ተሳታፊ ተገኝተዋል ብለዋል።

ከቱሪዝም ሳምንትና ኤግዚቢሽኑ ጎን ለጎን ፎረምና የፓናል ውይይቶች እንደሚካሄድ ጠቅሰው፣ የቱሪዝም ሳምንቱና ኤግዚቢሽኑ የእርስ በዕርስ የባህል ትውውቅ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

ለ4ኛ ጊዜ የተዘጋጀው የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንትና ኢግዚቢሽን ከመስከረም 21 እስከ 23 እንደሚካሄድም ጠቁመዋል።

በመርሃግብሩ ላይ የኦሮሚያ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ከፍያለው ተፈራ ፣የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማን ጨምሮ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋና ሌሎች የክልልና የፌዴራል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።


አምባሳደር ኢርቪን ማሲንጋ

# አሜሪካ ለኢትዮጵያ እያደረገች ያለውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታወቀች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ መንግሥት እና ሕዝብ ለኢትዮጵያውያን እያደረገ ያለው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኢርቪን ማሲንጋ ገለጹ።

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት (ዩኤስኤይድ) ባለፉት አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ የድጋፍ ፕሮግራም የተመዘገቡ ውጤቶችን በመግለፅና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የፓናል ውይይት በማድረግ የፕሮግራሙን የማጠቃለያ መርሀግብር ከትናንት በስቲያ አካሂዷል።

በማጠቃለያ መርሀግብሩ ላይ የተገኙት በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ኢርቪን ማሲንጋ እንደገለፁት፤ የአሜሪካ መንግሥት እና ሕዝብ ለኢትዮጵያውያን እያደረገ ያለው ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ከግጭት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን፣ የሠብዓዊ ድጋፎችን፣ ሰላማዊ እና ገንቢ ውይይቶችን በማድረግ ግጭቶችን ከማስቆም አኳያ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በግጭት ምክንያት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታዎች ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማድረጉንና በዚህም በኢትዮጵያ የድጋፍ ፕሮግራም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የጠቀሱት አምባሳደሩ፤ በርካታ ትምህርት ቤቶችንም በመገንባት በግጭቱ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መመለስ መቻሉን ተናግረዋል።

እንዲሁም ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች በአእምሯዊ ጤና እና በሥነ-ልቦና ድጋፍ መርሃ ግብር አማካኝነት ለመፍታት የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ተሰማርተው እየሠሩ እንደሚገኝ የጠቆሙት አምባሳደር ኢርቪን፤ በአንዳንድ አካባቢዎች ዜጎች ወደ መደበኛ ሕይወት እየተመለሱ እንደሚገኝ አንስተዋል።

የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት በኢትዮጵያ በግብርና፣ በአገልግሎትና በተለያዩ መስኮች እያደረገ ያለውን ተሳትፎ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ድጋፍ ፕሮግራም ሲኒየር ፕሮግራም አማካሪ ሊዲያ ጌታሁን በበኩላቸው፤ ፕሮግራሙ የአምስት ዓመት ቆይታ የነበረው ሲሆን በቆይታውም 174 ከሚደርሱ አጋር አካላት ጋር መሥራት መቻሉን በመግለጽ፤ በአማራ፣ ኦሮሚያና ትግራይ ክልሎች ላይ ቢሮዎችን በመክፈት ሴቶችንና ወጣቶችን ለማብቃት ከሚሠሩ ሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር በጋራ መሥራቱን አንስተዋል።

እንደ ፕሮግራም አማካሪዋ ገለጻ፤ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በተለይም ግጭት በተካሄደባቸው አካባቢዎች እንደ ቤተ-መጽሀፍት፣ የወጣቶች ማዕከልና በሌሎችም ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ሥፍራዎች የማደስ ተግባር ተከናውኗል። ከእነዚህም መካከል የአምቦ፣ ነቀምት፣ መቀሌና ሌሎችም ቤተ-መጽሐፍት ይገኙበታል።

ባለፉት አምስት ዓመታትም 375 ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ በፕሮግራሙ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉንም ፕሮግራም አማካሪዋ ጠቁመዋል።

ከግጭት ጋር የተያያዙ ጉዳቶችን በአእምሯዊ ጤና እና በሥነ-ልቦና ድጋፍ መርሃ ግብር አማካኝነት ለመፍታት በተደረገው ጥረት በተገኙ ተሞክሮዎች ዙሪያ የፓናል ውይይት ተደርጓል።

በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች በአስደንጋጭ ገጠመኞች በመሰቃየት ላይ የሚገኙ በርካታ ዜጎች ይገኛሉ። በዚህም በዜጎቹ ላይ የደረሰውን የሥነልቦና ቀውስ ለማከም አመቺ ሁኔታዎች ባይኖሩም ኢትዮጵያውያን ያላቸውን ባህላዊና ሃማኖታዊ መስተጋብሮችን በመጠቀም ችግሮቹን ለመቀነስ ጥረት መደረጉ ተገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢሬቻ በዓልን በሰላም!

ከአዲስ ዓመት መግቢያ አንስቶ እስከ አሁን በሀገሪቱ በርካታ የአደባባይ በዓላት ተከብረዋል፤ እየተከበሩም ነው። በዚህም በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አዲስ ዓመታቸውን፣ ሌሎች ደግሞ የመስቀል ደመራ በዓልን በደማቅ ሥነ ሥርዓት አክብረዋል።

እነዚህ በዓላት በአደባባይ የሚከበሩና ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው ናቸው። በበዓላቱም ላይ ከሕፃናት አንስቶ እስከ አዛውንት፣ በሀገር ውስጥ ከሚኖሩት ውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ይሳተፋሉ። በእዚህ ላይ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው የውጭ ሀገር ጎብኚዎችም በዓላቱን ሲሉ ወደ ሀገሪቱ ይመጣሉ። እነዚህ ጎብኚዎች አዲስ አበባን ብቻ የሚጎበኙ አይደሉም፤ በዓላቱ በሚከበሩባቸው የተለያዩ ክልሎች ይሄዳሉ።

ይህ ኢትዮጵያውያን ወደ ትውልድ ሥፍራቸው ጭምር እየተንቀሳቀሱ ቤተሰቦቻቸውን የሚጠይቁበት፣ የሚደግፉበት፣ በአጸፋው እነሱም የሚመረቁበት ወቅት፣ መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ ፋይዳውም ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል።

ሀገሪቱም እነዚህ በዓላት ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ በሚገባ እንዲታይና ለሀገራዊ ጥቅም እንዲውል በተለይ ለቱሪዝም ዘርፍ ያላቸውን ከፍተኛ ፋይዳ በመገንዘብ በትኩረት እየሠራች መሆኑ ይታወቃል። በተለይ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ በትኩረት እየሰራች እንደመሆኗ ይህ ወር ለዘርፉ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ ታምኖበትም በስፋት እየተሰራ ነው።

የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ሀገራቸውን እንዲያውቁ፣ የውጭ ቱሪስቶች ሀገሪቱን እንዲጎበኙ እና የሀገሪቱ አምባሳደር እንዲሆኑ ይፈለጋል፤ በጉብኝታቸው ከፍተኛ ሀብት የሚንቀሳቀስ እንደመሆኑም ከዚህ ሀብት ለመጠቀምም ጽኑ ፍላጎት አለ፤ ፍላጎት ብቻም ሳይሆን ከዚህ እምቅ ሀብት ለመጠቀም በርካታ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው። ይህ ተጠቃሚነት ይበልጥ እንዲሰፋም የጉብኝታቸው ቆይታ የተራዘመ እንዲሆን ይፈለጋል፤ ይህ እንዲሆንም በስፋት እየተሠራም ነው።

እነዚህ በዓላት ያለ ምንም የጸጥታ ችግር በሰላም እንዲከበሩ ማድረግ ይጠበቃል። ለዚህም ነው መንግሥት ሁሌም በዓላቱ ያለ ምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበሩ ልዩ ዝግጅት እያደረገ ሲሠራ የቆየው፤ እየሠራ የሚገኘውም።

ለዚህም ነው የመስቀል ደመራ በዓልን ጨምሮ እስከ አሁን በክልሎች የተለያዩ አካባቢዎች የተከበሩት የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የአዲስ ዓመትና የመስቀል በዓላት በሰላም ያለ ምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበሩ ማድረግ የተቻለው።

ብዝሀነት መልኳም ልኳም በሆነባት ኢትዮጵያ እነዚህ በዓላት ያለ ምንም የጸጥታ ችግር መከበር መቻላቸው መንግሥት ምን ያህል በሰላም ላይ እየሠራ መሆኑን በሚገባ ያመለክታል። መንግሥት በተለያዩ በዓላት ወቅትም ይህንን ያደርጋል። የመስከረም ወር ግን ከእነዚህ በዓላት ወቅቶች ይለያል፤ በዚህ ወር አንድ እና ሁለት በዓላት ብቻ አይደሉም የሚከበሩት፤ በርካታ በዓላት ናቸው። እነዚህ በዓላት ሁሉ ያለ ምንም የጸጥታ ችግር መከበራቸው መንግሥት ሰላምና ደህንነትን ለማረጋገጥ ምን ያህል እየተጋ መሆኑን ያረጋግጣል።

መንግሥትን ይህን ሲያደርግ የጸጥታ ኃይሎችን ብቻ ይዞ አይደለም፤ የሰላሙ ባለቤት ነው ብሎ በጽኑ የሚያምንበትን ሕዝብ ለእዚህ ዓላማ በማሳለፍም መሆኑ ይታወቃል። የበዓላቱ በሰላም መከበር ሲታሰብ ሕዝቡ የበዓሉም የሰላሙም ባለቤት እንደመሆኑ በዓላቱ በሰላም እንዲከበሩ ሙሉ አቅሙን ተጠቅሞ ሰርቷል ብሎ መግለጽ ይቻላል።

ይህ ለሰላም ያለ ቁርጠኝነትና ሰላምን የመጠበቅ ተሞክሮ በቀጣይ ሳምንት የኦሮሞ ብሔረሰብ ፈጣሪውን በሚያመሰግንበት የእሬቻ በዓል በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔና በቢሾፍቱ ሆራ አርሰዴ እንዲሁም በመላ ኦሮሚያ ክልልና በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች እንዲሁ እንደሚደገም ይጠበቃል።

ይህንንም በዓል በሰላም ያለ ምንም የጸጥታ ችግር ለማክበር የጸጥታ አካላት አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገዋል። ሕዝቡም ይህ ለሁለት ቀናት የሚከበር በዓል ያለ ምንም የጸጥታ ችግር እንዲከበር አስተዋጽኦ በማድረግ በኩል የማይተካ ሚና እንዳለው ይገነዘባል።

የበዓሉ ታዳሚዎች ከመላ ሀገሪቱ እንዲሁም ከውጭ ሀገሮች ወደ አዲስ አበባና ቢሾፍቱ በመንቀሳቀስ በዓሉን የሚያከብሩ እንደመሆናቸው በተለያዩ አካባቢዎች ጉዞ በሚያደርጉባቸው ወቅቶች እንዲሁም በበዓላቱ ወቅቶች የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት በሚንቀሳቀሱባቸው ሥፍራዎችና በሚያደርጓቸው የቆይታ ወቅቶች ሁሉ ሰላማቸው እንዲጠበቅ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም ሕዝቡ በየደረጃው ካለው የአስተዳደር መዋቅር እንዲሁም ከጸጥታ አካላት ጋር በመሆን ይህን ኃላፊነቱን መወጣቱን ማጠናከር ይኖርበታል።

የበዓላቱ በሰላም መከበር ፋይዳው ብዙ ነው። አንዱ በዓላቱ በተለመደው አግባብ ከተለመደውም አግባብ በላይ በድምቀት እንዲከበሩ ማስቻል ነው። ሌላው ደግሞ እነዚህ በዓላት ለሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑ ነው። የሀገር ገጽታ የሚገነባበት አንዱ መንገድ መሆኑም ይታመናል። እነዚህና ሌሎች የበዓላቱ መከበር ዓላማዎች በሚገባ እንዲሳኩ ዋናው መሳሪያ ሰላምና ሰላም ነው። በዓላቱ ያለ ምንም የጸጥታ ችግር የተከበሩበት ሁኔታ በዚህ ሳምንት በሚከበረው የእሬቻ በዓልም ላይ መደገም ይኖርበታል!

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አዲስ አበባ የዓለም ሦስተኛ የዲፕሎማሲ ማዕከል መሆኗን በተጨባጭ የሚያረጋግጡ ዐሻራዎች

**በጋዜጤኛና ሲኒየር የኮሙኒኬሽን ባለሙያ ሳንዱዘር አሥራት**

**የኮሪደር ልማትን ጨምሮ በከተማዋ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የከተማ ልማት ዕቅዶች አሁናዊ አፈጻጸም፤ ጀምሮ በጥብቅ ዲስፕሊን ተቀናጅቶ የመጨረስን አዲሰ የፕሮጀክት አመራር ልምድ በሀገር አቀፍ ደረጃ እያስተዋወቀ ያለ መሆኑ ተደጋግሞ በየደረጃው ባሉ የሥራ ኃላፊዎች ይነገራል**

አዲስ አበባ መጠሪያ ስያሜዋን ያገኘችው እቴጌ ጣይቱ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፰፻፸፱ (1879) ዓ/ም ፍልውሃ፤ ፊል-ፊል ወደሚልበት መስክ ወርደው ሳሉ ከዚህ ቀደም አይተዋት የማያውቋት አንዲት ልዩ አበባ አይተው ስለማረከቻቸው ቦታውን «አዲስ አበባ!» ሲሉ ጠርተውታል በሚል የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

ከእንጦጦ ተራራዎች ግርጌ የተቆረቆረችው አዲስ አበባ፤ ከባሕር ጠለል በላይ በ2500 ሜትር ከፍታ ላይ የምትገኘም ነች። ከአሜሪካዋ ኒዮርክና ከኒዘር ላንዷ ጀኔቫ ከተማ በመቀጠል ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ውሳኔዎች የሚተላለፉባት ፤ የዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆናም እያገለገለች ትገኛለች። የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከመሆኗም ባሻገር የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫ ፤ የባለ ብዙ የትብብር መድረክ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን ጨምሮ የዓለም የዲፕሎማቲክ ልዑካን መሰብሰቢያና መኖሪያም ጭምር ነች።

የከተማ አስተዳደር ማዕረግ እንዲኖራት ሆና አስቀድማ የተዋቀረች ቢሆንም ከአንድ ምዕተ-ዓመት ለሚበልጥ ጊዜ በአዝጋሚ የለውጥ ሂደት ውስጥ መሰንበቷ በበርካቶች ይነገራል። ከምስረታዋ ጊዜ አንስቶ ከተማዋ፤ በአዝጋሚ የለውጥ ሂደት አልፋ አሁን ወደምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ላይ መድረሷ አጀንዳ ሆኖ የማያከራክረን ቢሆንም በወርሀ መጋቢት 2010 ዓ.ም በሀገሪቱ የተደረገውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ ወሳኝ የገፅታ ግንባታና ፈጣን የስማርት ሲቲ የሪፎርም ተግባራትን በጊዜ የለንም መንፈስ እያከናወነች ትገኛለች፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ፤ በመንግሥታት የለውጥ ሂደት ለዘመናት የልማት ሥራዎችን በሚፈለገው ፍጥነትና ጊዜ ጀምሮ መጨረስ፤ አዳዲስ የልማት ሥራዎችን ደረጃ በደረጃ መጀመርን ጨምሮ ቅንጅታዊ የፕሮጀክት አመራር ውስንነት በጉልህ የሚስተዋል ከመሆንም አልፎ በየአካባቢው የብሶትና የሕዝባዊ ቁጣም ምንጭ የነበረ መሆኑ አያጠያይቅም።

በተለያዩ ጊዜያት ብክነትና ምዝበራን ጨምሮ፤ ሌሎችም በተጓዳኝ የተስተዋሉ ችግሮች ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎችና ምሁራን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ተደጋጋሚ ወቀሳ የሰነዘሩባቸው ጉዳዮች መሆናቸውም የሚዘነጋ አይደለም። ለዚህም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ጨምሮ፤ ሌሎችም ወሳኝ ሀገራዊ ሜጋ ፕሮጀክቶች የገጠማቸው የፕሮጀክት አመራር ችግርና ምዝበራ በዋቢነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በከተማዋ ምዝበራና ብልሹ አሰራርን ጨምሮ ሌሎችም በፕሮጀክት አመራር ወቅት በጉልህ ሲስተዋሉ ከነበሩ ችግሮች ትምህርት በመውሰድና ማስተካከያ በማድረግም ጭምር በፕሮጀክቶች አመራር ላይ ጀምሮ መጨረስን ማዕከል ያደረጉ አበረታች መሻሻሎች በመታየት ላይ ናቸው፡፡

ከተደረገው የመንግሥት ለውጥ ወዲህ፤ ከተማ አስተዳደሩ የነዋሪውን ሁለንተናዊ የልማት ተጠቃሚነትን ጨምሮ በምርጫ ወቅት ለሕዝቡ የገባቸውን ቃል ደረጃ በደረጃ በተግባር ለመፈጸም እንዲያስችለው ዘርፈ ብዙ የከተማ ልማት ዕቅዶችን ፤ ጊዜ በወሰዱ ጥናቶች ለይቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በሁሉም ረገድ ከተማዋ ወደ ፈጣን የለውጥ ሂደት እንድትገባ ለማስቻል እየተወሰዱ ያሉ የሪፎርም ርምጃዎችን ተከትሎ ከ60ና 90 ቀናት ባጠረ ጊዜ በርካታ ወሳኝ የልማት ሥራዎች ባልተለመደ መልኩ በከተማዋ በተጨባጭ መታየት ጀምረዋል።

በአንድ የምርጫ ዘመን እንኳን፤ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ተፈጽመው የማያውቁ የልማት ሥራዎች ከለውጡ በኋላ ከ60ና 90 ቀናት ባጠረ ጊዜ ተፈጽመው፤ ለታለመላቸው ሕዝባዊ አገልግሎት በየበጀት ዓመቱ ክፍት በመደረግ ላይ መሆናቸውን ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2016 ዓ.ም አጠቃላይ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርትን ለከተማው ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት አሃዛዊ መረጃዎችን በማነጻጸር አስረድተዋል፡፡

የከተማዋን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ገጽታና ደረጃ በሚፈለገው ልክ ማሻሻል እንዲቻል በሁሉም ረገድ እየተከናወኑ ያሉ የስማርት ሲቲ የከተማ ልማት የሪፎርም ተግባራት ፤ በጥብቅ የፕሮጀክት አመረር ዲስፕሊን ከ60ና 90 ቀናት ባጠረ ጊዜ ተጠናቀው ለታለመላቸው ሕዝባዊ አገልግሎት ክፍት በመደረግ ላይ መሆናቸው በከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ በስፋት የሚታወቅ ነው፡፡

ከወትሮ በተለየ በከተማዋ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የስማርት ሲቲ የከተማ ልማት ተግባራት፤ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ጨምሮ የሌሎች ሀገራትን የከተማ ልማት ልምድና ተሞክሮ ከከተማዋ አሁናዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም የሚተገበሩ ከመሆናቸውም ባሻገር በሰው ተኮር የልማት መርህ የነዋሪዎችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ የሚከናወኑም ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ በሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በኩል ማብራሪያ ተሰጥቶበታል።

ለዚህም ከንቲባ አዳነች አቤቤ “ልማትን የምንሰራው ለሰው ነው ተግባራዊ የምናደርገውም ሰውነትን በሚያስቀድም መርህ ነው” በሚል የሚያደርጓቸውን ንግግሮች በዋቢነት መውሰድ ይቻላል። የሪፎርም ሥራው የከተማዋን የዲፕሎማሲ፤ የቱሪዝም፤ የኮንፍረስ፤ የኢንቨስትመንት፤ የጤና፤ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማዕከልነት በተጨባጭ ማረጋገጥን ቀዳሚ ኢላማ ያደረገ መሆኑም በተለያዩ ጊዜያት እየተነገረ ያለ ነው።

24/7 ባለፉት ጊዚያት ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት የተደረጉ የኮሪደር ልማት ሥራዎች፤ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎች ፤ ዓለም አቀፍ የኮንፈረንስ ማዕከላት፤ ማሻሻያ የተደረገባቸውን ጨምሮ እንደ አዲስ ተገንብተው ለሕዝባዊ አገልግሎት ክፍት በመደረግ ላይ ያሉ የጤና መሠረተ-ልማቶች ፤ የኢንቨስትመንት እና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች እንዲሁም ሌሎችም መሰል ተግባራት በአጠቃላይ በከተማዋ የስማርት ሲት የከተማ ልማት ፕሮግራም ማዕቀፍ ተግባራዊ የሚደረጉ መሆናቸውን አስቀድሞ ከተማ አስተዳደሩ ይፋ ተደርጓል። አተገባበሩም ይህንኑ የተከተለ መሆኑ ለከተማዋ ነዋሪዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ሁሉ የሚታይ ነው።

የኮሪደር ልማትን ጨምሮ በከተማዋ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የከተማ ልማት ዕቅዶች አሁናዊ አፈጻጸም፤ ጀምሮ በጥብቅ ዲስፕሊን ተቀናጅቶ የመጨረስን አዲሰ የፕሮጀክት አመራር ልምድ በሀገር አቀፍ ደረጃ እያስተዋወቀ ያለ መሆኑ ተደጋግሞ በየደረጃው ባሉ የሥራ ኃላፊዎች ይነገራል። በሁሉም ረገድ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች በይበልጥ በጊዜ የለንም መንፈስ ተጠናክረው የሚቀጥሉ ስለመሆናቸው ከንቲባ አዳነች በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ አጽንኦት ሰጥተው ሲናገሩም ተደምጠዋል።

ለዚህም ተጨባጭ ማሳያ የሚሆነው በአንድ የምርጫ ዘመን እንኳን በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ተፈጽመው የማያውቁ የልማት ሥራዎች ከስልሳና ዘጠና ቀናት ባጠረ ጊዜ፤ ተጠናቀው ለታለመላቸው ሕዝባዊ አገልግሎት ክፍት መደረግ የመቻላቸው ጉዳይ ነው። ለአብነት ያክል በከተማ አስተዳደሩ በተከታታይ ዓመታት ተገንብተው ለአገልግሎት ብቁ የተደረጉ ወደ 30 ሺ ገደማ ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ፤ የነዋሪውን የኑሮ ጫና በዘላቂነት የሚያቃልሉ ናቸው ተብለው በአዋጪነት ጥናት ተለይተው ተግባራዊ የተደረጉ ስለመሆናቸው ብዙ ተብሏል፡፡

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ተጠየቅ

# "140 የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ተከታትለናል፤ ፕሮጀክቶቹ ከጊዜና ከዋጋ ጋር በተያያዘ በጣም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ናቸው"

- ኢንጂነር መስፍን ነገዎ
የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር


ፎቶ- አሸናፊ ጉደታ

**በምርመራና መልካም አስተዳደር ቡድን**

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ውጤታማ ለማድረግ ቁልፍ ዓላማ ይዞ የተቋቋመ መንግሥታዊ ተቋም ነው። የኮንስትራክሽን ዘርፉ በዋጋ፤ በጥራት፤ በጊዜ እና በአካባቢ ደህንነት ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል ትልቅ ተልዕኮ ወስዶ እየሰራ ያለ ነው።

በዛሬው የተጠየቅ ዓምዳችን በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ያለበትን ወቅታዊ ሁኔታ፣ እያጋጠሙት ባሉ ተግዳሮቶች ዙሪያ የባለሥልጣኑን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር መስፍን ነገዎ አነጋግረን በሁለት ተከታታይ ክፍሎች ለአንባቢዎቻችን የምናቀርብ ሲሆን፤ ክፍል አንድ እነሆ፡-

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣን እና ኃላፊነት አኳያ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**ኢንጂነር መስፍን፡-** እንደ ተቋም በዋናነት አምስት ሥራዎች አሉን። የመጀመሪያው ጥናት እና ዝግጅት ነው። ጥናትና ዝግጅት ሲባል ኮድና ስታንዳርድ ያጠናል፤ ያዘጋጃል፤ ወደ ሥራ እንዲገባ ያደርጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሰራር ሥርዓቶችና ዘዴዎችን በማጥናት ወደ ሥራ እንዲገባ የሚያደርግ ነው።

ሁለተኛው የምዝገባ እና ሰርቲፊኬሽን ሥራ ነው። በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚሳተፉትን ባለሙያዎች፣ ኩባንያዎችና ማሽነሪዎች ይመዘግባል፤ ሰርቲፊኬሽን ይሠጣል፤ በሶስተኛነት የቁጥጥር ሥራ ይሰራል። ስታንዳርዶች ሥራ ላይ እንዴት እንደዋሉ ይቆጣጠራል። ይህ ማለት ሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያወጣውን የሕግ ማዕቀፍ ኮድና እና ስታንደር ጨምሮ እንዴት እንደሚተገበር ይቆጣጠራል።

ተቋሙ ከዚህ በተጨማሪ «ሬጉላቶሪ ኮምፒሊያንስ» ይሰራል። ሌላው ቁጥጥር ደግሞ በተለይ በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ላይ ኮድ እና ስታንዳርድን በተመለከተ የፌዴራል ፕሮጀክቶች አሰራሮች ጋር በትክክል ስታንዳርድ ዲዛይን ተደርገው መሰራታቸው ይመረምራል። የሚስተካከል ነገር ካለ እንዲስተካከል ካልሆነ ግን ወደ ተግባር እንዲሄድ የሚያስችሉ ሥራዎችን ይሰራል።

በፌዴራል ደረጃ ያለውን የዲዛይን ክለሳ በተለይ የፌዴራል መንግሥት ስፖንሰር የሚያደርጋቸውን ፕሮጀክቶች እኛ (ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ) እንሰራለን። ይህ ከቁጥጥር አካል አንጻር የሚታይ ነው። ሌላው ደግሞ እነዚህ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ከገቡ በኋላ በዲዛይንና በውል መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላል።

በተጨማሪም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚፈጠሩ ውዝግቦችን ይፈታል። ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውዝግብ ይበዛበታል። አንዳንድ ጊዜ የሚፈጠሩ ውዝግቦች ወደ ፍርድ ቤት ይሄድና 15 እና 20 ዓመት ድረስ ይቆያል። በዚህ ወቅት የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን በአማራጭ የውዝግብ አፈታት ሥርዓት ችግሮች እንዲፈቱ ያደረጋል።

ይህ አሰራር በፊት ያልነበረና አዲስ ትግበራ ላይ የዋለ አሰራር ነው። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ አሰራሩን ተግባራዊ ለማድረግ ባለፈው ዓመት የማደራጀት እና የአሰራር ሥርዓቶችን የማስተካከል ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። አሁን ወደ ሥራ ገብተን አንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ ተሳክቶልናል። አንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ ግን ከሕግ ክፍተት አለ፡፡

በባለሥልጣኑ አዋጅ 1237 የሚፈቅደው ለኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርና ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ብቻ ነው። ስለዚህ መሥሪያ ቤቶች ጋር ተያይዞ አሁን ላይ ዓቃቤ ሕግ መሥራት አትችሉም በማለቱ ሕጉ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ነገር ግን አጠቃላይ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚፈጠሩ ውዝግቦችን የመፍታት ስልጣን ለኮንስትራክሽን ባለስልጣን ተሰጥቷል። በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ካልተፈታ ወደ ፍርድ ቤት ይሄዳል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2016 በጀት ዓመት ምን አቅዳችሁ ምን አሳካችሁ? በ2017 በጀት ዓመት ምን አቅዳችሁ እየሰራችሁ ነው?**

**ኢንጂነር መስፍን፡-** በ2016 በጀት ዓመት በርካታ እቅዶች ነበሩን። ዋና ዋናዎቹ ግን ከዝግጅት እና ጥናት ጋር ተያይዞ ሁለት ክፍተቶች ነበሩ። እነሱም ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ስናጠና ቆይተናል፤ አሁን ላይ ጥናቱ ወደ ማጠቃለያው የደረሰ ሲሆን ይህን ለመተግባር የሚያስችል ሶፍትዌር እየበለጸገ ነው።

የሶፍትዌር ልማት ከምንለው አንደኛው የኮንስትራክሽን ዋጋ ጥናት ነው። ከዚህ ቀደም በነበረው አካሄድ እያንዳንዱን አማካሪ ወይም «ኮንሶልታንት» የሚሰራው እንደፈለገ በራሱ መንገድ ነበር። ምክንያቱም በሳይንሱ በርካታ የአሰራር ስልቶች በመኖራቸው እና በሀገራችን እነዚህን ስልቶች የሚመራ አሰራር ስላልነበረ ነው፡፡

አንዳንድ ሀገራት በራሳቸው አሰራሩን የሚመራ አሰራር ይኖራቸዋል። በእኛ ሀገር ግን አሰራሩ ስላልነበረ ልቅ ነበር አማካሪ ድርጅቶች እንደፈለጉ ሲሆኑ ቆይተዋል። አሁን ላይ ግን አስጠንተን መመሪያ እየወጣ ነው። ከጸደቀ በኋላ ወደ ሥራ እንገባለን። ይህም ወጥ የሆነ የኮንስትራክሽን ግምት አሰራር ለማውጣት ያግዛል። የኮንስትራክሽን ዋጋ ተገማችነት እንዲኖር ያስችላል።

ሌላው በባለፈው ዓመት በዋነኝነት የሥራ ነው የፕሮጀክቶች የሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ መገመቻ እና ፐርፎርማንሳቸውን የሚመዝን ሶፍትዌር እየተዘጋጀ ነው። አማካሪዎች ብዙ ጊዜ የሚያደርጉት ትልልቁንም ትንንሹንም ፕሮጀክት በአስራ ስምንት ወር እንደሚጠናቀቅ ይገልጻሉ። ሶስት እና ከዚያ በላይ ዓመት የሚፈጀውን ፕሮጀክት በአስራ ስምንት ወር ይጠናቀቃል ይላሉ። አማካሪዎቹ ፕሮጀክቶች በ18 ወራት እንደማይጠናቀቅ እያወቁ በ18 ወራት እንጨርሳለን የሚሉት በእኛ ሀገር ሕግ ፕሮጀክት ከተጀመረ ከ12 እስከ 18 ወራት በኋላ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ስለሚፈቀድ ነው። እነዚህ ወራቶች ከመሙላታቸው በፊት ግን የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ ሕጉ አይፈቅድም። በመሆኑም ውል ከታሰረ በኋላ ኮንትራክተሮቹም ፕሮጀክቱ በተቀመጠለት ጊዜ እንዳይጀመር ምክንያቶችን ይደረድራሉ።

ብዙ ጊዜ ኮንትራክተሮች ሥራ ሲጀምሩ የሥራ መጀመሪያ ጊዜውን በማጓተት ሶስተኛ ወር ወይም ከሶስት ወር በኋላ እንዲጀመር ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ በተባለለት ጊዜ እንዳይጨርሱ ያደርጋቸዋል፤ የዋጋ ማስተካከያም እንዲጠይቁ በር ይከፍትላቸዋል። ይህን ችግር ለመፍታት እንዲቻል የፕሮጀክቶችን ዋጋ እንደሚገምተው ሶፍትዌር ዓይነት እያንዳንዱን ማለትም ጊዜውንም የሚመራ ሶፍትዌርና ማንዋል እየተጠና ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ቀደም የሊፍት ስታንዳርድ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ «ኦፕሽናል» ነበር። አሁን ላይ ራሱን የቻለ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ወደ ማስገደድ ልንሄድ ነው። ምክንያቱም አሁን ላይ በአዲስ አበባ የሕንፃዎች ርዝመት እስከ 48 ፎቅ ደርሷል፤ በዲዛይን ደረጃ ደግሞ ከ63 እስከ 73 ድረስ እየመጣ ነው።

እንደሚታወቀው ሊፍት ማለት «ቨርቲካል ትራንስፖርቴሽን» ነው። (ወደ ላይ እና ወደ ታች የሚደረግ ትራንስፖርት ዓይነት ነው፡፡) ወደ ጎን ለሚሄዱት ትራንስፖርቴሽን አገልግሎት ለሚሰጡ እንደ ባጃጆችን እና ትናንሽ ተሽከርካሪዎች ሳይቀር አስገዳጅ ቦሎ (አካል ምርመራ) እና ለሹፌሮችም የብቃት ማረጋገጫ እየሰጠን ባለንበት በዚህ ወቅት ለሊፍቶች ግን ምንም ዓይነት የብቃት ማረጋገጫ እና ስታንዳርድ የለንም።

ከሊፍት ጋር ተያይዞ የሌሎች ሀገራትን ስናይ የሊፍቱን ጤንነቱን የሚከታተል ቴክኒሽያን ይኖራል፤ ሊፍቱ ጤነኛ ነው ወይስ አይደለም ለሚለውም ራሱን የቻለ ስታንዳርድ አለው። በስታንዳርዱ መሰረት ጤንነቱ በየዓመቱ እየተፈተሸ ልክ እንደተሽከርካሪ «ቦሎ» ይደረጋል። ይህንን እንቅስቃሴ ወደ አስገዳጅነት እንዲሻገር ለማድረግ ከደረጃዎች ኢንስቲትዩት ጋር በመነጋገር በጋራ እየሰራን ነው። በጥሩ ሂደት ላይም እንገኛለን፤ ስታንዳርዱ ለቴክኒክ ኮሚቴ ቀርቦ ለማጸድቅ በሂደት ላይ ነው፡፡

ከምዝገባና ሰርቲፊኬሽን አኳያ ያቀድናቸው እቅዶች አሉ፤ መሻሻል ያለባቸው አንዳንድ ቅሬታዎችን ለመፍታት በ2017 ዓ.ም ላይ እንደ ትልቅ ሥራ ይዘነዋል። ከዲዛይን ክለሳ ጋር በተያያዘ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የመጡትን ዲዛይኖች ሪቪው አድርገን መልሰናል። የተገኙ ግኝቶችን በሶስት ክፍልን ማየት እንችላለን። አንደኛው ዋጋ ማጋነን አለው። ሁለተኛው ደግሞ በስታንዳርዱ መሰረት ዲዛይን አለማየት ችግር ነው። ሶስተኛው ዲዛይኖቹ «ናሽናል ኮፒታቲቭ» መሆን ሲገባቸው «ኢንተርናሽናል ኮምፒታቲቭ» ሆነው ቀርበዋል።

ይህ ማለት በፕሮጀክቱ ውስብስብነትና በፕሮጀክቱ የዋጋ ከፍታ የዓለም አቀፍ ጨረታ እንዲሆን ነው። ዓለም አቀፍ ጨረታ ሲሆን ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የእኛን ሀገር ኩባንያዎች መወዳደር ይችላሉ። ስለዚህ ይህን የማስተካል ሥራ ሰርተናል።

ከቁጥጥር አንጻር በሕጎች እና በኮዶቹ አተገባበር ላይ በስፋት የሕግ ጥሰቶች ስለሚፈጸሙ በ10 ከተሞች በርካታ ሥራዎችን ሰርተናል። ችግሩን ከክልል መንግሥታቶች እና ከተማ አስተዳደር ጋር ተነጋግረን የምናስተካክለው ቢሆንም በተለይ አዋጅ 624ን ከመተላለፍ አኳያ ችግሮች በስፋት ይታያሉ።

ለምሳሌ አዲስ አበባን ብትወስዱ ከጂ+5 በላይ የሆኑ ህንጻዎች ሲገነቡ ባለው ሂደት ከሕጉ አንጻር መወጣጫቸው መሆን የሚገባው ከብረት የተሰራ ነው። ነገር ግን አዲስ አበባ ላይ በግንባታ ሂደት ለሚገኙ ህንጻዎች መወጣጫ የባህር ዛፍ አጠናን ይጠቀማሉ። በዚህ የተነሳ በቅርቡ ቦሌ ሁለት ሰዎች ወድቀዋል። በተመሳሳይ ካርል አደባባይ አካባቢ በሊፍት ውስጥ በሚሠራ ሥራ የወደቁ አሉ። በአዲስ አበባ ከመወጣጫ ብረቶች ስታንዳርድ ጋር ክፍተቶች አሉ። ከዚህ በመነሳት ለአዲስ አበባ ቁጥጥር እና ዲዛይን ባለሥልጣን ስለ ስታንዳርዱ ግብረ መልስ ሰጥተን ችግሮቹ እንዲስተካከል ተደርጓል።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በሕግ ተቆጥሮ ከተሰጡት ሥራዎች መካከል ፕሮጀክቶችን መቆጣጠር ነው። ከዚህ አንጻር ባለፈው ዓመት 140 የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ተከታትለናል። ለብዙዎቹ ወዲያውኑ ግብረ መልስ ሰጥተናል። በተመለከትናቸው ፕሮጀክቶች ላይ በተለይም ከጊዜና ከዋጋ ጋር በጣም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ናቸው። ለዚህም ዋና ምክንያቱ አንደኛው ዋጋ የሚቀያየረው ቶሎ ነው፤ በዚህም የዋጋ ማስተካከያ ይጠይቃሉ። ሁለተኛው ክፍያ ጠይቀው ሶስት እና አራት ክፍያ ሳይከፈላቸው በአሰሪ መሥሪያ ቤት የቆየባቸው በስፋት አሉ። እንደዚህ ዓይነት ግኝቶች ተገኝተዋል።

ባለፈው ዓመት ከሰራናቸው ሥራዎች መካከል የኮንስርሽን ኦዲት ነው። በዚህም በአምስት ፕሮጀክቶች ላይ የኮንስትራክሽን ኦዲት ሰርተናል። ነገር ግን የኦዲት ሥራው ያላለቀ ስለሆነ ውጤቱ ገና ነው። እሱ ካለቀ ግን ወደ ሕግ የሚሄድም ጉዳዮች አሉት። ከአሰራር ሥርዓት ጋር በተያያዘ ባለፈው ዓመት ለሽልማት በቅተን ነበር።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የ2016 ዓ.ም የዲጂታል ትገበራ ተቋም (dijitale inablede institution) ኢትዮ ስታንዳርድ ተሸልመናል። ይህም 26 የሚሆኑ አገልግሎቶችን በኦንላይን በመስጠት የተገኘ ሽልማት ነው። የግዥ ሥርዓቱን በተቀመጠው የሀገሪቱ ሕግ መሠረት በማከናወን ካሉት ተቋማት ሁለተኛ ደረጃን ይዘን አጠናቀናል። «ኢፍ ሚስን» በመጠቀም ወይም በፋይናንስ ኤሌክትሮኒክስ ሲስተም ሙሉ በሙሉ በመጠቀም በሚል አቢሲኒያም ሽልማት አበርክቶልናል። ይህ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ጥሩ ስኬት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በበጀት ዓመቱ በተቋሙ የሥራ እንቅስቃሴ ያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**ኢንጂነር መስፍን፡-** ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤታችን ኦዲት አድርጎ ነበር። እሱ ላይ የምንቀበላቸውና የማንቀበላቸው ክፍተቶች ነበሩ። ለምሳሌ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት 41 ፕሮጀክቶችን ኦዲት አድርጓል። ከነዚህ ፕሮጀክቶች ግማሾቹ በፍርድ ቤት ቆመዋል፤ ግማሾቹ ደግሞ ፋይናንስ የሚደርጋቸው አካል አቋርጧቸዋል። ግሚሶቹ ደግሞ እኛ ከመመስረታችን በፊት ከ12 እስከ 15 ዓመት የቆዩ ናቸው።

እነሱ እንደ ግኝት የወሰዱት ተፈጠሩ የተባሉ ችግሮችን ለገንዘብ ሚኒስቴር በደብዳቤ ማሳወቅ ነበረባችሁ የሚል ነው። ለገንዘብ ሚኒስቴር አሳወቃችሁ ለፕሮጀክቶቹ አንድም በጀት ተሰጥቶ እንዲቀጥል ካልሆነም እንዲቋረጥ ማድረግ ነበረባቸው በሚል ነው። ይህንን እንደ ግኝት በመቁጠር መንግሥት ለኪሳራ ተዳርጓል በሚል ዋና ኦዲተር ጉዳዩን ፓርላማ አቅርቧል።

ሌላው እንደ ክፍተት የምናየው እንደሚታወቀው የፕሮጀክት ቁጥጥሩን የምናገኘው በምንፈልገው ልክ አይደለም። ለምሳሌ የመገጭን ፕሮጀክት ብንወስድ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

## “140 የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ተከታትለናል፤ ፕሮጀክቶቹ…

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

20 ዓመት ቆይቷል። በ20 ዓመታት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን መረጃ ማግኘት በጣም ከባድ ነው። ቢገኝም በጣም የተቆራረጠ መረጃ ነው። አንዳንዶቹ የፐርፎርማንስ ቦንድ ያስያዙ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የውል ጊዜያቸውም ያለፈባቸው ናቸው።

በዚህ ሳቢያም ርምጃ ለመውሰድ እንደገናም ተጠያቂ ለማድረግ ደንበኛው የሚጠበቅበትን ክትትል ካላደረገ ወደ ፍርድ ቤት በሚሄድበት ጊዜ የሚያሸንፈው ኮንትራክተሩ ነው። በዚህም የተነሳ አንዳንዶቹ ወደ ፍርድ ቤትም ሄደው ገና አላለቁም። ግን የፍርድ ሂደቱ የሚያሳየው ኮንትራክተሮች እንደሚያሸንፉ ነው። ይህ የሚመነጨው መረጃ ባለመኖሩ ነው።

ለዚህ መፍትሔ እንዲኖር ባለፈው ዓመት የመረጃ ቋት እንዲኖር ሥራ ጀምረን ነበር። ነገር ግን መንግሥት በአንድ ቦታ ነው የሚለማው ብሎ ስላቆመው የመረጃ ቋት የማልማት ሂደቱ ተቋረጠ። ይሁንና እንደገና የመረጃ ቋት የማልማት ሂደቱ ባለፈው ዓመት ሰባተኛ ወር ላይ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ተፈቀደልን።

ሌላው በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ከሚስተዋሉ ችግሮች መካከል ትልቁ ክፍተት የአቅም ጉዳይ ነው። አንደኛ ሎጂስቲክስ፤ ሁለተኛ በጀት፤ ሶስተኛ የሰው ኃይል ነው። እኛ ጋር ያለው የሰው ኃይል እንደ እኔ ተሾመ የተቀመጠ ካልሆነ በስተቀር አቅም ያላቸው ባለሙያዎች የተሻለ አማራጭ ሲያገኙ እየለቀቁብን ነው። የመልቀቃቸው መንስኤ ሁለት ነው። የመጀመሪያው እንደ ተሸከርካሪ እና መሰል አቅርቦት ችግር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ደሞዝ ነው።

ለምሳሌ ከእኛ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የወጡ አስራ ሁለት ባለሙያዎች ሌላ መሥሪያ ቤት የተቀጠሩት ከ70 እስከ 80 ሺህ ብር በላይ ነው። ሰሞኑም እንዲሁ ሁለት ባለሙያዎች ከመሥሪያ ቤታችን ለቀዋል። ሌላ መሥሪያ ቤት ሄደው የተቀጠሩት በሁለት መቶ ሺህ ብር ነው። ስለዚህ እኛ ጋር የሚቀረው ተወዳዳሪ ያልሆነና አቅም ክፍተት ያለበት ነው። በርካታ ባለሙያዎች ከለቀቁ የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ከገበያ መሳብ ይኖርብናል፤ ከገበያ ለመሳብ ደግሞ የተሻለ ደሞዝ ማቅረብን ይጠይቃል።

አሁን ላይ ከገንዘቡ እና ከሎጂስቲኩም በከፋ የሰው ኃይል ችግር አለብን። ችግሩን ለመቅረፍ ለሠራተኞቻችን በየጊዜው ስልጠና በመስጠት አቅም ከማሳደግ ሥራዎች በተጨማሪ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶችንም እየዘረጋን ነው። ለምሳሌ ባለሙያው ሄዶ መረጃ ሰብስቦ በሙያው የሚያደርገውን የቀን ተቀን ሃሳብ መለዋወጥን ባሕል ብናደርግ ችግሩን መቅረፍ እንችላለን የሚል ነው። ሁለተኛ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር ተነጋግረን በአዲሱ ፐብሊክ ሪፎርም ጥያቄዎችን ለመመለስ እየሰራን ነው።

ሌላው ያለብን ችግር ደግሞ የአሰራር አቅም ችግር ነው። እኛ ከመጣን በኋላ የተሰሩ የአሰራር ሥርዓቶች አሉ። ለምሳሌ ከሥራ ባሕልና ደረጃ ጋር ብንወስድ ‹‹ኮንክሪት ካስት›› የሚያደርግ ቡድን ምን ያህል በቀን ያመርታል የሚለውን ስታንዳርድ የተሰራው የዛሬ 35 ዓመት ነው። በዚህ ዘመን ትልቁ ፕሮጀክት ጂ+1 ነው። የአሰራር ሥነ ዘዴውም ቢሆን ከ30 ዓመት በፊትና አሁን አንድ አይደለም። አምና እና ዘንድሮ እንኳን አንድ ዓይነት አይደለም። እኛ እስከምንመጣ ድረስ ኢንዱስትሪው የአረጀ የአሰራር ሂደት ሲጠቀም ነበር። ይህ ደግሞ መንግሥትን ይጎዳል። አሁን ላይ ግን ቴክኖሎጂ ስለ ዘመነ አዳዲስ እና ሥራን የሚያቀሉ እንዲሁም ጥራትን የሚጨምሩ ማሽኖች መጥተዋል። ይህ አሰራራችንን ማዘመን እንድንችል አስችሎናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስልጠና የሰጣችኋቸው ሠራተኞች የሚለቁ ከሆነ ብቁ ባለሙያ ከማፍራት ረገድ ችግር አይኖርም ወይ? እንዴት ነው ማሳካት የምትፈልጉትን እቅድ እውን ማድረግ የሚቻለው?**

**ኢንጂነር መስፍን፡-** እስከዛሬ አሰልጥነናቸው መሥሪያ ቤታችንን የለቀቁ ሠራተኞች የሉም። ለሠራተኞቻችን አጫጭር ስልጠናዎች ነው የምንሰጠው። ስልጠናዎችን በራሳችን እና ከኮንትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር እንሰጣለን። ከኮንትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የምንሰጠው ስልጠና ፕሮፌሽናል ፕሮጀክት ማኔጅመንት ሰርተፍኬሽን ነው። ይህ ሰርተፍኬት ዓለም አቀፍ ነው። ይህን ስልጠና ከወሰዱ ባለሙያዎቻችን አንዱ ብቻ መሥሪያ ቤታችን ለቋል።

ይሁን እንጂ አሁንም ሌሎቹ ትልቅ ደመወዝ ከእኛ ይጠብቃሉ። እነዚህን ባለሙያዎች ቅጥር ከመከልከሉ በፊት ከገበያ የቀጠርናቸው ናቸው። ከእነዚህ ባለሙያዎች አብዛኞዎቹ የተወሰነ ሰርተው በዚያው የጠፉት ሲሆን ግማሾቹ እንደውም አልመጡም። ክሪላንስ ያዞሩትም በኋላ ነው። አንዳንዶቹ ትርፍ ሥራ የሚሰሩ እና በጊዜ የማይገቡ በመሆናቸው ከሥራ አሰናብናቸዋል። በወር ሁለት ሶስት ጊዜም አይገቡም። ሌሎቹ ግን እኛ ገንዘብ እና ጉልበት ያወጣንባቸውና ሥራ የተለቀቁ የሉም። እንደ ሕግ አንድ ሠራተኛ እንደሚለቅ ከሶስት ወር በፊት ቀድሞ ካሳወቀ መከልከል አይቻልም። አሁን ላይ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ከ140 በላይ ሠራተኞችን ይፈልጋል። ከ140 በላይ ለሚሆኑ ሠራተኞች ክፍት የሥራ ቦታ አለን።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በ2017 በጀት ዓመት ምን ለማሳካት አቅዶ ሥራ ጀመረ?**

**ኢንጂነር መስፍን፡-** ከ10 ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ አንጻር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ አምስት ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች አሉት። እነዚህን እቅዶች እውን ለማድረግ ከ100 በላይ ተግባራትን እናከናውናለን። ከእነዚህ ውስጥ አምስቱን ብገልጽ፤ አንደኛው የሙስና ግመታዊ ማመላከቻውን ከፍ ማድረግ ነው። ይህ ሲዘጋጅ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ 96ኛ ነበረች። ባለፈው ዓመት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የ‹‹ኮስት ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ›› ባወጣው መረጃ ከ96 ወደ 94 ዝቅ ብሏል። ይህም የሙስና ወንጀል እንደ ሀገር የተወሰነ መሻሻሉን የሚያሳይ ነው። ነገር ግን እንደ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት መሰራት የነበረባቸው እና እኛ በሰራናቸው ጥብቅና ተከታታይነት ያላቸው ሥራዎች ሙስናን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ እንድችል ረድቶናል።

ለምሳሌ በኦንላይን አገልግሎት አንደኛ በመውጣት እውቅና ያገኘነው ከ46 ተቋም መካከል ነው። ነገር ግን እስካሁን በሲስተሙ እኔ እራሴ ቅሬታ አለኝ። ለምሳሌ በኦንላይን ቀጠሮ ተሰጥቶት ከሩቅ ቦታ የመጣ ደንበኛ ከእኛ የሚፈለገውን አገልግሎት ለማግኘት የተወሰነ ነገር ሲቀር መብራት ሊጠፋ ይችላል። ብዙ ሰዓት ጠብቆ አገልግሎቱን ለመጨረስ የተወሰነ ሲቀረው መብራት ከጠፋ እና ሥራው ከተቋረጠ ደንበኛው ይበሳጫል። በ2017 የበጀት ዓመት ይህን ችግር ለመቅረፍ የአቅም የማሳደግ ሥራ ተሰርቷል።

ቴሌ በጀመረው ክላውድ አገልግሎትም ቅሬታ አለን። የአንዱን ሰው ዳታ አንዱ ጋር ይወስዳል። በዚህ ምክንያት ደንበኞቻችን ተከፍተውብናል። የእኛ ዓላማ ቀጠሮ ላይ ሀሜት ስላለ እዚያው አመልክቶ እዚያው የሚስተናገድበትን መንገድ መፍጠር ነው። እንደ ብሔራዊ መታወቂያ እዚያው በአካባቢው የሚወሰድብት፤ ደንበኛው ማደስም ከሆነ እዚያው ታድሶልሃል እንዲባል፤ አዲስም ከሆነ ‹‹አውተንትኬት›› አድርጎ ዶክመንቱን መውሰድ እንዲችል ነው። ይህም በውጭ ሀገር ያሉ ነገር ግን በሀገራችን ኩባንያ ያላቸው ሰዎች ባሉበት ሀገር ሆነው የፈለጉትን መሥራት እንዲችሉ የሚያደርጋቸው ሲሆን ይህም የደንበኛውን እርካታ ከፍ ያደርጋል።

በዚህ ዓመት ያሰብነው አውቶ ማሽኑን ከመጨረሳችን በፊት ዩኒቨርሲቲዎች ስለሚታወቁ ተማሪ እኛ ጋር መጥቶ የተመረቀበትን ዶክመንቱን እናያለን። በኢንጂነሪንግ ትምህርት የሚያስመርቁትን ሰኔቱ ካፀደቀላቸውና ከምርቃቱ በፊት ሲልኩልን ምላሽ እንልክላቸዋለን። ተማሪዎቹ ወደ ተቋሙ መምጣት ሳይጠበቅባቸው ዩኒቨርሲቲው ሰብስቦ ይልክልናል። ከእነ ፖስታው ከዲግሪያቸው ጋር ይሰጣቸዋል። ይህ አሰራር እዚህ ጋር ያለውን ሰልፍ ያስቀራል።

ሌላው ያሰብነው የኢትዮጵያ የዲጂታላይዜሽን ፓርት የኮንስትራክሽን ሪጉላይታይዜሽን የመረጃ ቋት ሲሆን የሚለማው ከኢንሳ ጋር በመተባበር ነው። አሁን ላይ ውል ገብተን ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን ፕሮጀክቱ የ11 ወር ነው። ይህ ዘጠኝ ሞጁሎች ያሉት ነው። ከዘጠኙ ሞጁሎች ውስጥ አንደኛው የቁጥጥር ነው። የኮምፒሊየንስ ቁጥጥር እና የፕሮጀክት አስተዳደር ቁጥጥር ነው። ይህ የሚሆነው በየቀኑ ከየፕሮጀክቱ መረጃ የሚይዝ ሲሆን በየጊዜው ደግሞ ሪፖርት አድርግልኝ ሲባል ሪፖርት ያደርጋል። ለምሳሌ ሁለት ሺህ ፕሮጀክቶች ቢኖሩ በወሩ መጨረሻ ላይ የሁለት ሺህ ፕሮጀክት አፈጻጸም በየወሩ እያስቀመጠ ይሄዳል፡፡

ድርጅቶች ግብር ላይ የሚያስመዘግብው ዝቅ ያለ ነው። እኛ ጋር የሚያመጣ ደግሞ ከፍተኛ ስለምንፈልግ ከፍ ያለ ያስመዘግባሉ። ይህን እንዲጣራ የምናደርገው ደብዳቤ በመፃፃፍ ነው። መፃፃፉ ደግሞ ዛሬ ይሄዳል፤ የዛሬ ሳምንት ወይ የዛሬ ሁለት ሳምንት ይመጣል። አገልግሎት ፈላጊው ደግሞ ዛሬ ነው እምፈልገው በሚል ቅሬታ እንዲፈጠር ያደርጋል። ከእኛም ጋር ሳያረጋግጡ እንዳለ ወስዶ የመስጠት ሁኔታ ይስተዋላል። ይህን ሲያደርጉ የያዝናቸው አሉ። ከውጭም ደግሞ እስኪ አጣሩልን ብለው አምጥተው የተያዙ አሉ።

አሁን ላይ በግንኙነት ሞጁል ገቢዎች ሚኒስቴር፤ ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክ፤ ዩኒቨርስቲዎች ከእኛ መሥሪያ ቤት እና ከንግድ እና ቀጠናዊ ሚኒስቴር ጋር ይተሳሰራሉ። ለምሳሌ መስፍን ካምፓኒ የሚል አንድ ካምፓኒ ቢኖር የዚህን ሁሉ አጣርቶ እውነተኛ የሆነውን ይሰጠናል። ገቢዎች ጋርም ሆነ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ጋር መዋሸት አይችልም። ዝቅ አድርጎ ያስገባ ከሆነ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣንም ጋር ዝቅ አድርጎ ይመዘግባል። ማሽነሪው ምን ዓይነት አቅም አለው የሚለውን ስለተሳሰረ ያንኑ መረጃ ያመጣል።

ሁለተኛ የዚህ ሲስተም ትልቁ ጥቅም የሞባይል መተግበሪያ አለው። ለምሳሌ መዋቅር ሲወድቅ አንድ ሰው ካየ ሪፖርት ማድረግ ይችላል። አሁን ግን ለምሳሌ ሰው ወድቆ ሰው ሞቶ ሪፖርቱ ቶሎ አይመጣም። ከፖሊስ ምርመራ በኋላ፤ ከዜና በኋላ ነው የምንሰማውና ምርመራ የምንጀምረው። አሁን ግን ማንም ሲሰራ እያንዳንዱ ሁነት ሪፖርት ያደርጋሉ።

ለአብነት የሴቶች ክፍያ ፔሮል ላይ የሚፈርሙት እና በእጅ ላይ የሚቀበሉት እኩል አይደለም ይባላል። ይሄን እራሷ የተጎዳችው ሴት በመተግበሪያው ሪፖርት ታደርጋለች። የእነሱ ደህንነት ይጠበቃል። ለእኛ ግን ሪፖርት ይደርሰናል። የሞባይል መተግበሪያው ገጠራማ በሆኑ አካባቢዎች የፕሮጀክት ማናጀሮች በተለይ ኔትዎርክ የሌለባቸው በሞባይል መተግበሪያው ይጠቀማሉ። ችግሮች ይፈታሉ።

የትኛው ፕሮጀክት የፐርፎርማንስ ቦንዱ የሚቀጥለው ወር ይቃጠላል። መታደስ አለበት። ዛሬ ያላደሰ ማን ነው? የሚለውን ሪፖርት ያደርግልናል። አሁን ግን በቁጥጥር ምናልባት የዛሬ አምስት ዓመት ለቁጥጥር ስንሄድ ይሆናል የምናገኘው። ይሄ ደግሞ ከተበላሸ በኋላ ነው። ይሄ እንደ ትልቅ ግራንድ ፕሮጀክት ነው ዘንድሮ የወሰድነው፡፡

ሌላው ደግሞ 2017 ዓ.ም ግራንድ ብለን የምንወስደው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር የተፈራረምነው ፕሮጀክት አለ። ማሻሻያውን ጨምሮ የኮድ እና እስታንዳርድ አዲስ ጥናት አለው። ለምሳሌ ታሪኩን ስናይ የዛሬ ሰላሳ አምስት ዓመት የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ደረጃ ብቻ ነበር። ከአስር ዓመት በኋላ ወደ ዘጠኝ አደገ። የዛሬ አስር ዓመት አካባቢ ወደ አስራ ሁለት ያደገ ሲሆን አሁን ደግሞ ወደ ሰላሳ ልናሳድገው ነው፡፡

ከአሁን በፊት የነበረው የቴሌፎን እና ኤሌክትሪክ ብቻ ነው። ስለዚህ ኤሌክትሪክ ዲዛይን የሚሰራው አካል የ‹‹ኢንቢዩልት ፋይቨር ኔትዎርክ‹‹ አንድ እስታንዳርድ ይመጣል ማለት ነው። ለምሳሌ አሁን እዚህ ቤዝመንት ስልክ አይሰራም። ለምንድን ነው የማይሰራው፤ መንግሥት መንገድ እና ውጪ ላይ አልምቶታል። የግለሰቦች ህንጻ ውስጥ ግን የለም። አሁን የንግድ ባንክ ህንጻ ላይ ከተወሰኑ ፎቆች በላይ ኔትወርክ አይሰራም። ለእራሱ ኢንስቶል ማድረግ አለበት። ትልልቁ ህንፃ በሚወጣበት የህንጻው ባለቤት አልፈልግም ካለ እዛ ህንጻ ላይ የሚከራይ ሰው ኔትዎርክ አይኖረውም ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ‹‹ኢን ቢዩልት የፋይብር ኔትዎርክ›› አንዱ የኮድ አካል ሆኖ ይመጣል። የእሳት አደጋ በፊት ትልልቅ አልነበረም አሁን ግን የሚጠይቅ ነው። G+73 እና 90 ሲሰራ የራሱ ‹‹ፋየር ፋይቲንግ›› ሲስተም ይፈልጋል። ሁለተኛ ደግሞ የራሱ ድሮን ይፈልጋል።

ለምሳሌ እዚህ ቤት ውስጥ እሳት ቢነሳ ‹‹ኢም ቢሊት›› የሆነ ኢንፍራ ስትራክቸር የለውም። የሌለው እኛ አስገዳጅ ስላደረግነው ነው። ውጭ ሀገር እያንዳንዱ ቦታ ላይ ስፕሬን አለች። እሳት ሲነሳ የትም ሳይሄድ ያጠፋዋል። እነዚህ አስገዳጅ ሆነው ይመጣሉ፡፡

**/የቃለመጠይቁን ሁለተኛ ክፍል የዛሬ ሳምንት ይጠብቁ /**

**ወደ ጎን ለሚሄዱት ትራንስፖርቴሽን አገልግሎት ለሚሰጡ እንደ ባጃጆችን እና ትናንሽ ተሽከርካሪዎች ሳይቀር አስገዳጅ ቦሎ (አካል ምርመራ) እና ለሹፌሮችም የብቃት ማረጋገጫ እየሰጠን ባለንበት በዚህ ወቅት ለሊፍቶች ግን ምንም ዓይነት የብቃት ማረጋገጫ እና ስታንዳርድ የለንም**



# ለትውልድ መልካም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አረጋውያንን ማክበርና ፍቅር መስጠት ሀገር ወዳድነት ነው።

አረጋውያን ለሀገር ብዙ ውለታ ውለዋል፤ የዋሉትንም ውለታ መዘከር፤ ማከበርና ፍቅር መስጠት ተገቢ ነው ብለዋል።

አረጋውያን የተሰጣቸውን ሃላፊነት በመወጣት መልካም እሴት ለትውልድ ጥለው አልፈዋል፤ ለጣሉትና ለሰሩት መልካም ሥራ ክብራቸውንና መብታቸውን ማከበርና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ፍቅርና ክብር ለአረጋውያን መስጠት የዜጎች ግዴታ ነው፤ ለእነሱ ክብርና ፍቅር መስጠት ሀገርን መውደድ ነው፤ ሀገርን የሚወድ ማንኛውም ዜጋ መልካም እሴት የሰጡትን አባቶች መደገፍ አለበት ሲሉም አብራርተዋል።

አረጋውያንን ደስተኛ ማድረግ መልካምነት ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ መልካምነት ደግሞ የኢትዮጵያውያን ባህል በመሆኑ በዚሁ እሴት የመደገፍ ሥራ መሥራት ተገቢ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ምንም ጧሪና ቀባሪ የሌላቸውን አረጋውያንን ለመደገፍ ራሱን የቻለ ሥርዓት እየተዘረጋ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በበጎ ፍቃድ በማህበር ተደራጅተው የአረጋውያን ጉዳይ ላይ የሚሠሩ ማዕከላትን፣ ግለሰቦችን የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ይበልጥ እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል።

አረጋውያንን ለመደገፍ በጎ ፍቃድ ሥራ የተሠማሩ የተለያዩ ማህበራትን የማበረታታትና አስፈላጊውን ግብዓት የማሟላት ሥራ እየሠራ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

አረጋውያን በመደገፍ ለትውልድ መልካም እሴትን የማተላለፍ ሥራ እየተሠራ ነው፤ በድጋፉም የመሥራት አቅም ያላቸውን ጉልበት የማይጠይቁ ሙያዊ ነገሮችን እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፤ ጡረታ የወጡትንም በሙያቸው ተደራጅተው አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመድን ፈንድ ፅህፈት ቤት በማቋቋም አረጋውያንን የመደገፍ ሥራ እየሠራ እንደሆነም ገልጸዋል።

በስጋጃና መሰል ሙያዎች በርካታ አረጋውያንን የማሳተፍ ሥራ እየተሠራ ነው፤ በተለያዩ ሙያዎች አረጋውያንን ለማሳተፍ ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው፤ ተጠናክሮም ይቀጥላል ሲሉ ጠቁመዋል።

በየክልሎች ምንም የገቢ ምንጭ የሌላቸው አረጋውያንን የገቢ ምንጭ የሚያገኙበት የሥራ እድል በመፍጠር የነፍስ ወከፍ ገቢ የሚያገኙበት መንገድ የመፍጠር ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አረጋውያንን በፋይናንስና በቴክኒክ መደገፍ፤ መሥራት ለሚችሉት የሥራ እድል መፍጠር ለሀገር ሁለተናዊ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

ለአረጋውያን እየተደረገ ያለው በፋይናንስ የመደገፍ፤ የማቋቋም፣ ምቹ የሥራ እድል የመፍጠር ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው፤ ተጠናክሮም ይቀጥላል ሲሉ ጠቁመዋል።

የዓለም አረጋውያን ቀን በጋምቤላ ክልል « ክብርና ፍቅር ለአረጋውያን» በሚል መሪ ቃል በዓለም ለ34ኛ፤ በኢትዮጵያ ለ33ኛ ጊዜ በትናትናው ዕለት ተከብሮ ውሏል።

# የሰላም ስብራቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፈቃድና በቆራጥነት ግንባር ለግንባር ተገናኝተን ለመነጋገር ስንችል ነው ያሉት ፕሮፌሰር አድማሱ፤ የሚያስፈልገን ሀገራችን የሁላችንም መሆኗን ተገንዝበን ችግሮቻችንን ለማሸነፍ በፈቃደኝነትና በቆራጥነት በጋራ መታገል ስንችል ነው ብለዋል።

“የኢትዮጵያ ሕዝብ የሠለጠነ፣ ሰላም ወዳድና ጨዋ መሆኑን ደግመን ደጋግመን ሰምተናል፤ አይተናልም” የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ ከዚህ ሕዝብ የወጡ የተለያዩ ዓላማዎችን ይዘው በፖለቲካ ቡድንነት የተደራጁ ወገኖቻችን በቅን ልቦና ከታገሉና ካታገሉ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመጥን የፖለቲካ ሥርዓት ለማምጣት ብቃት ይኖራቸዋል። ለሀገርና ለሕዝብ የሚያገለግል፣ ለአሁኑም ሆነ ለሚቀጥሉት ትውልድ የሚበጅ ሥርዓት መሠረት በመጣል ታሪክ መሥራት ይችላሉ ነው የሚሉት።

ጸሐፊው እንደሚገልጹት፤ የግል ወይም የቡድን ጥላቻና ጠብ በሀገር ጉዳይ ውስጥ ቦታ የላቸውም። ይበጃል ያሉትን የተለያየ ሃሳብ ይዘው በሀገር ጉዳይ ላይ የሚነጋገሩ ሰዎች በሀገር ጉዳይ የሚተባበሩ፣ ይበጃል ያሉትን ሃሳብ በሥራ ላይ ለማዋል የሚፈለገውን ሥልጣን ለማግኘት የሚፎካከሩ እንጂ ጠላቶች መሆን አይገባቸውም። የሥልጣን ተፎካካሪዎች ዓላማ የተሻለ ሁኔታ ለማምጣት፣ ሃሳብ ለሃሳብ መፋጨት፣ እንጂ መጠፋፋት አይደለም። ዓላማቸው ሃሳባቸውን ለሕዝብ አቅርበው በሕዝብ ዳኝነት መሠረት በሰላም ሁሉም እንደ ድርሻቸው ሥልጣንን መጋራት መሆን አለበት።

የሕዝብ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሰዎች ይህንን እውን ለማድረግ ቅን መንፈስ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። መነጋገርን ትተው የመጠፋፋትን መንገድ ከገፉበት አደጋው ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር መሆኑን መገንዘብ አለባቸው ሲሉም ያሳስባሉ።

የሃሳቦች መለያየት በራሱ ክፉ ነገር ሳይሆን ለሀገር እድገት የሚበጁ ሃሳቦችን ለማፍለቅ መነሻ (ጥንስስ) መሆኑ ሊታወቅ ይገባል የሚሉት ፕሮፌሰር አድማሱ፤ ሃሳቦችን እርስ በርሳቸው በማፋጨት፣ ብሎም በማቀራረብ፣ በጋራ ለጋራ የሚሆኑ አማራጭ ሃሳቦች በመፍጠር ወገንን ማገልገል እንደሚቻል ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያዊ ጨዋነትንና አብሮ የመኖር ባህላችንን ስንቅ አድርገን፣ የመግባባት ዴሞክራሲን መንገድ አቅጣጫ ይዘን ከተጓዝን እኛም ሰላም እናገኛለን፣ መጪዎቹም ትውልዶች ይኮሩብናል ሲሉም ከሀገራዊ ምክክሩ ብዙ ማትረፍ እንደሚቻል ጽፈዋል።

የፖለቲካ ተመራማሪው ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) በበኩላቸው “ከአንድ ቀን ጦርነት የአስር ዓመት ውይይት የሚል ታዋቂ አባባል አለ። እኛም እስካሁን በጦርነቶችና በግጭቶች ብዙ ነገሮች ሞክረናል። እስካሁን እንዳየነው ወደ ጦርነትና ግጭት የሚያመሩ ሰዎች መነሻና መድረሻቸውን የማያውቁና ግልጽ ፕሮግራም የሌላቸው ናቸው” ይላሉ።

በጣም የተደበላለቁ ነገሮች አሉ። ሁሉም ተንስቶ ፖለቲከኛ ነኝ የሚልበት በእውቀት የማንመራበት፤ አዋቂዎቻችንን ሽማግሌዎቻችንን የማናዳምጥበት ደረጃ ላይ ደርሰናል የሚሉት ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር)፤ ይሄ ሁኔታ ሄዶ ሄዶ ይረግባል። ሲረግብና ስንደማመጥ ወደ ማዕከል እንመጣለን። ፍጹማዊ አንድነቱም ፍጹማዊ ልዩነቱም ይቀራል። ልዩነት ቢኖረንም ከውይይትና ከምክክር አያልፍም ወደሚል እምነት እንሻገራለን ብለው እንደሚያምኑ ይናገራሉ።

ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ያስቀመጣቸው አጀንዳዎች ሲዘረጉና ወደ ውይይት ሲገባ ልዩነቶቻችን ብዙ እንዳልሆኑ ሁሉም ሰው እንደሚረዳ የሚጠቁሙት የፖለቲካ ተመራማሪው፤ እኛ እንደ ምሁር ብዙ መድረኮችን መርተን አወያይተናል፤ መጨረሻ ላይ አለመነጋገርና አለመወያየታችን እንጂ ልዩነታችን ጠባብ አንድነታችን ደግሞ የሚገዝፍ መሆኑን ተረድተን እንወጣለን ነው የሚሉት።

መግባባት ላይ ሊደረስባቸው የሚገቡ ሰንደቅ ዓላማ፣ ሕገመንግሥት፣ የመሬት ይዞታ፣ የክልል አከላለል እና ሌሎችም ጠንከር ያሉ ጉዳዮች እንዳሉ አመላክተው፤ እነዚህ ሁሉ ነገሮች በሀገራዊ ምክክሩ ለውይይት ቀርበው በውይይት የሚፈቱት በዚሁ መንገድ እንዲፈቱ፤ ወደ ሪፈረንደም የሚሄዱ ጉዳዮችም በሕዝብ ድምጽ መቋጫ እንደሚያገኙ ይገልጻሉ።

ብዙ ዓመት ብንወያይ ችግሮቻችንን እየፈታን በጋራም ሆነ በግል በሰዎች እና ንብረት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት እየቀነስን ሀገረ መንግሥት እየገነባን የምንሄድበትን ዕድል እንፈጥራለን እንጂ የምናጣው ነገር አይኖርም ሲሉም ያክላሉ።

የተከበሩ ተስፋዬ በልጂጌ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሥራ የማያልቅ ተግባር ነው። በትውልዶች ቅብብሎሽ እየተሳካ የሚሄድ፤ ከዘመን ወደ ዘመን ከጊዜ ወደ ጊዜ ትውልዶች በደረሱበት ደረጃና ዘመኑ በሚጠይቀው ሁኔታ ማዕከል ሀገራቸውን እየገነቡ የሚቀጥሉበት ነው። በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ አለመግባባት እንዲፈጠር በማድረግ በየጊዜው ሀገራችንን ለትርምስ፣ ለግጭት እና ለጦርነት እየዳረጉ የመጡ ጉዳዮችን ቁጭ ብለን ለመነጋገር የጀመርነው ጉዞ የሀገረ መንግሥት ግንባታን የሚያሳልጥ ነው ይላሉ።

የረጅም ዘመን ታሪክ ያለን እና በዓለም ላይ በሥልጣኔያችን የምንታወቅ ግንባር ቀደም ሀገር ሆነን አንዳንድ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በቀላሉ እንደ ሀገር የመቀጠል ህልውናችንን ጭምር የሚፈታተን ደረጃ የሚደርስበት አንዱና ዋና ምክንያት የጋራ መግባባት ላይ ያልደረስንባቸው በርካታ ነገሮች በመኖራቸው መሆኑንም ይገልጻሉ።

አንዱ የማንግባባበት ጉዳይ ያለፈው ታሪካችን መሆኑን በአብነትነት አንስተው፤ በሀገራችን ታሪክ የሚጻፍበትም ሆነ የሚተረክበት መንገድ ሀገር በሚገነባ አቅጣጫ ሳይሆን ሀገርን ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ በሚከት መንገድ ነው። ከታሪካችን ጋር ተያይዞ ትናንት በሆነ ጉዳይ መጨቃጨቅ ትተን ከትናንት ትምህርት ወስደን ዛሬን የተሻለ ለማድረግ እና ነገን በትክክለኛ አቅጣጫ ለመጓዝ መግባባት ላይ መድረስ የምንችለው ቁጭ ብለን መነጋገር ስንችል ነው ይላሉ።

የልዩነት ሃሳቦቻችንን ወደ መድረክ አምጥተን ተነጋግረንባቸው መግባባት ካቃተን ሕዝብ ይወስንባቸዋል፤ ሀገር የሚገነባው በዚህ አቅጣጫ ነው የሚሉት ፖለቲከኛው፤ ዛሬ የሚያጨቃጭቁንን፣ የሚያዋጉንን፣ የሚጋጩንን፣ የሚያባሉንን እና እንዳንተማመን የሚያደርጉንን ጉዳዮች በመነጋገር፣ በመወያየት እና በመመካከር በማረም መግባባት ላይ መድረስ ከቻልን ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ለመገንባት በሚያስችል አቅጣጫ መጓዝ እንችላለን በማለት ሀገራዊ ምክክሩ ትልቅ ዕድል ይዞ መምጣቱን ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያውያን ያለፈው ታሪካችን ሲታይ የጦርነትና የግጭት ብቻ ሳይሆን አኩሪ የሆነ ሥልጣኔ፣ አብሮነት፣ አንድነት፣ ወንድማማችነት እና በረጅሙ ታሪካችን ያካበትነው የጋራ ማንነት ያለን ማህበረሰቦች ስለሆንን አለመግባባቶቻችንን በሠለጠነ መንገድ በውይይት በመፍታት አንድነታችንን ማጽናት አለብን ሲሉም ይመክራሉ።

ችግር ውስጥ የገቡ ሀገራት ቁጭ ብለው ተነጋግረው ስህተቶቻቸውን አርመው ሁሉንም ወገኖች ያሳተፈ ትክክለኛ አቅጣጫ ተከትለው ዜጎች በእኩልነት ኮርተው የሚኖሩበት ሀገር መፍጠር መቻላቸውን አውስተው፤ ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን የሚዲያ ሰዎች፣ ፖለቲከኞች፣ አክቲቪስቶች፣ ምሁራን፣ አሰላሳዮች እና ጸሀፊዎች ብሔራዊ መግባባት ላይ እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል።

# የኢሬቻው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ኦሮሞ የባህል አልባሳት ተውበው ይስተዋላሉ።

እነዚህ አልባሳት በዓላቱን ከማድመቅ ባለፈም የአንድን ማህበረሰብ ማንነት በማጉላትና በማስተዋወቅ ፣ ኢኮኖሚውን በማሳደግ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የኢሬቻ በዓል መቃረብን አስመልክቶ የባህል አልባሳት ገበያው ምን ይመስላል ሲል የኦሮሞ ባህል አልባሳት ዲዛይነሮችንና ሸማቾችን አነጋግሯል።

የሎቲ ፋሽን ባለቤትና የፋሽን ዲዛይነር መርሲሜ ኩምሳ እንደምትለው የኦሮሞ ባህል አልባሳት ዲዛይነሮች ሥራዎቻቸውን ለመሸጥ በዓመቱ የሚጠብቁት ትልቁ በዓል ኢሬቻ ነው። ከዚህ አንጻር ከሌሎች በዓላት በበለጠ ብዙ ትዕዛዞችን የሚቀበሉበትና ትልቅ ሽያጭ የሚኖርበት ወቅት ነው ትላለች።

ኢሬቻ በየዓመቱ አዳዲስ የፋሽን ስልቶች የሚታዩበት በዓል እየሆነ መጥቷል የምትለው መሪሲሜ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም አልባሳቱ ባህላዊ እሴታቸውን በጠበቀ መልኩ በተለያየ ስልት የሚሠሩ በመሆናቸው ልብሱን የሚፈልግ ሰው እየጨመረ መምጣቱን ታነሳለች።

ዲዛይነሯ የሁሉም የኦሮሞ አካባቢ አልባሳትን የምትሠራ ሲሆን የአልባሳቱ ዋጋም እንደየዲዛይኑ ይለያያል። ለአብነትም በሎቲ ፋሽን የወለጋ የባህል ልብስ በሶስት ሺ ብር እየተሸጠ ሲሆን በጥልፍ ሲሠራ ደግሞ እስከ ሰላሳ ሺ የሚደርስ ዋጋ እንደሚኖራቸው ትገልጻለች።

በኢሬቻ ከአልባሳት በተጨማሪ የተለያዩ የኦሮሞ ማህበረሰብን ማንነት የሚገልጹ እንደ ቦራቲ ፣ሀደ ስንቄ ቆሪ የሚባሉ በእጅ የሚያዙ ጌጣጌጦችን እያቀረበች መሆኑ ትገልጻለች።

አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ ባህልና ቋንቋ ከማሳደግ አንጻር የሚኖረው ሚና ትልቅ መሆኑን የምታነሳው መሪሲሜ፤ በኢሬቻ በዓላት የሚስተዋሉ የተለያዩ አልባሳትም የየአካባቢውን ባህል እያስተዋወቁና የሌላ ብሄር ተወላጅ የሆኑ ሰዎች እንኳን ስለ ማህበረሰቡ የተወሰነ እውቀት እንዲጨብጡ እያደረገ ይገኛል ትላለች።

ሌላኛዋ ለኢፕድ ሃሳቧን ያጋራችው የባህል አልባሳት ዲዛይነር አስናቁ መርሻ የባህል አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ ባህል አጉልቶ የማሳየት አቅም ያለው ነው ትላለች። ለአብነትም የኡዳ ዛፍ እንዲሁም ጥቁር ነጭና ቀይ ጥለት ያለው ልብስ የኦሮሞ ማህበረሰብ መገለጫ ሆኖ በህብረተቡ ዘንድ እንዲቀረጽ የሆነው ከምንም ነገር በላይ ሰዎች ለብሰውት በሚንቀሳቀሱ የባህል አልባሳት አማካኝነት ነው ትላለች።

ወ/ሮ አስናቁ የባህል አልባሳት ባህሉን ከማስተዋቅ በተጨማሪ ለብዙዎች የሥራ እድል እየፈጠራና ብዙዎች ቤተሰቦቻቸውን እንዲያስተዳድሩ በማድረግ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ሚና እንዳለውም ታነሳለች።

ዲዛይነሯ ከኢሬቻ መድረስ ጋር ተያይዞ በዙ ሰዎች በፈልጉት ዲዛይን አልባሳት እንዲሠራላቸው ወደ ሱቋ ጎራ ማለት መጀመራቸውን የገለጸች ሲሆን ከምትቀበለው ትእዛዝ በተጨማሪም ይፈለጋሉ ተብለው የሚታሰቡ አልባሳትን እየሠራች ለገበያ እያወጣች ትገኛለች።

ዲዛይነሯ አልባሳቱ ላይ ከአምናው የኢሬቻ በዓል ጋር ሲነጻጸር ብዙም የሚባል የዋጋ ልዩነት የለም ያለች ሲሆን ሸማቾች ወደ ሱቋ ሲመጡም ከ1500 እስከ ስምንት ሺ ብር ባለው ዋጋ የሚፈልጉትን አይነት የባህል ልብስ መግዛት እንደሚችሉ ትገልጻለች።

በባህል አልባሳት መሸጫ መደብር ውስጥ ለኢሬቻ በዓል የምትለብሰውን ቀሚስ ስታዝ ያገኘናት ወጣት ሴና የማነ እንደምትለው በየአመቱ የኢሬቻን በዓል ስታከብር የባህል አልባሳትን ለብሳ እንደሆነ ገልጻለች።

አምና የወለጋ አካባቢ ቀሚስን ለብሳ ማክበሯን የምታስታውስ ሲሆን ዘንድሮ ከጓደኞቿ ጋር አንድ አይነት በጥልፍ የተሠራ የአርሲ ቀሚስ ለብሰው ለመውጣት በመነጋገራቸው ለዚህም የሚያሰሩትን ቀሚስ መርጣ ትእዛዝ መስጠቷን ገልጻለች።

# ባሕልን ከማስተዋወቅ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው እየጎለበተ የመጣው ኢሬቻ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ በድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል እሬቻ አንዱ ነው። የክረምት ወቅት አልፎ የበጋው ወቅት ሲገባ በአዲስ ዓመት መባቻ መስከረም ወር ላይ ይከበራል። እሬቻ በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ በድምቀት የሚከበር በዓል ሲሆን፤ ብሔረሰቡ ለፈጣሪው ምስጋና የሚያቀርብበት ታላቅ ባሕላዊ እሴቱ ነው። በዚህም በዓል ብሔረሰቡ ፈጣሪውን ያመሰግንበታል፤ ዘመኑ የሰላም፣ የፍቅርና የአንድነት እንዲሆን ይመኝበታል።

ከዓመት ዓመት በደማቅ ሁኔታ እየተከበረ የመጣው የእሬቻ በዓል ዘንድሮም የፊታችን ቅዳሜና እሁድ በድምቀት ይከበራል። የ2017 ዓ.ም የእሬቻ በዓልን በደማቅ ሁኔታ ለማክበርም የተለያዩ ዝግጅቶች ተደርገዋል። ከዝግጅቶቹ መካከልም "እሬቻ ኤክስፖ 2017" አንዱ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው ይህ ታላቅ ዓመታዊ ዓውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል መስከረም 18 ቀን 2017 ዓ.ም የተከፈተ ሲሆን ለሰባት ተከታታይ ቀናት እንደሚቆይም የኦሮሚያ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ አስታውቋል።

የኦሮሚያ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ከሀገሬ ኢቨንት እና ፕሮሞሽን ጋር ያዘጋጀው ይህ ኢግዚቢሽንና ባዛር የኦሮሞ ብሔረሰብን ባሕል ከማስተዋወቅ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ አበርክቶው የጎላ ስለመሆኑም የኤግዚቢሽኑ ተሳታፊዎችም ገልጸዋል። ተሳታፊዎቹ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች የኦሮሞ ባሕልን ይገልጻሉ ያሏቸውን ባሕላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዲሁም ባሕላዊ ምግቦችንና መጠጦችንም ይዘው ቀርበዋል።

የዝግጅት ክፍላችንም ኤግዚቢሽኑን በጎበኘበት ወቅት የኦሮሞ ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግቦችና መጠጦችን ጨምሮ የተለያዩ አልባሳት፣ ጌጣጌጦችንና ቁሳቁስን በስፋት ተመልክቷል። የኦሮሞ ባሕላዊ የምግብ ዓይነቶችን እያስተዋወቁና እየሸጡ ካገኘናቸው መካከል ነጋ የኦሮሞ ባሕላዊ ምግብ አንዱ ነው። ድርጅቱ ባሕላዊ ምግቦችን እያዘጋጀ ለገበያ የሚያቀርበው በሁለት እህትማማቾች አማካኝነት መሆኑን ወይዘሮ ፀሐይ ለታ ትገልጻለች። ወይዘሮ ፀሐይ ከታናሽ እህቷ ጋር በመሆን በተለይ ተወልደው ያደጉበትን የወለጋ አካባቢ ባሕላዊ ምግቦችን እያዘጋጁ ለገበያ ያቀርባሉ፡፡

ወይዘሮ ፀሐይ እንዳብራራችው፤ እሷና እህቷ የሚያዘጋጇቸውንና የወለጋ አካባቢ መገለጫ ከሆኑት ባሕላዊ ምግቦች መካከል ጭኮ፣ አንጮቴ፣ ጮሮርሳ፣ ቆጭቆጫ፣ አካኢ ቆሪ፣ ጨጨብሳና ፉስፉሶን ይዘው በኢግዚቢሽኑ ቀርበዋል። ከባሕላዊ መጠጦቹም እንዲሁ የወለጋ ቡና እና ብርዝ ይገኝበታል። እነዚህን የኦሮሞ ባሕላዊ ምግቦችና መጠጦች በኤክስፖው ይዘው መቅረብ በመቻላቸው እጅግ ደስተኛ እንደሆኑም ገልጻለች፡፡

ወይዘሮ ፀሐይ እንዳለችው፤ የእሬቻ ኤክስፖ መዘጋጀቱ ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አለው። እሬቻ የሰላምና የአንድነት በዓል ነው። በተለይም የኦሮሞ ብሔረሰብ ከያለበት ተሰባስቦ ጨለማ ከሆነው የክረምት ወቅት ወደ ብርሃን ላሸጋገረው ፈጣሪው ታላቅና የከበረ ምስጋና የሚያቀርብበት እንደመሆኑ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያጠናክርና ከየአካባቢው የሚመጣውን ሕዝብ አንድ የሚያደርግ ነው።

ከማህበራዊ ጠቀሜታው ባለፈም ከዓመት ዓመት እየሰፋና እየደመቀ የመጣው የእሬቻ በዓል አከባበር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳውም ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል። የእሬቻ በዓል መገለጫ የሆኑና በዓሉን ያደምቃሉ የተባሉ የማህበረሰቡ ባሕላዊ ምግቦች፣ ቁሳቁስና አልባሳት በዚህ ወቅት በስፋት ወደ ገበያ ይወጣሉ። ይህም ለኢኮኖሚው የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ ነው። ባሕላዊ አልባሳቱን፣ ጌጣጌጦቹንና ባሕላዊ ምግቦቹን ከማስተዋወቅ ባለፈ በመሸጥ ለሚተዳደሩ ሰዎች አንድ የንግድ/ ቢዝነስ/ አማራጭ ሆኖ እያገለገለ ነው። ለበርካቶች የሥራ ዕድል እየፈጠረም ይገኛል። በተለይም ዘንድሮ የሚከበረው የእሬቻ በዓል "እሬቻ ኤክስፖ 2017" በሚል ለመጀመሪያ ጊዜ ኤግዚቢሽንና ባዛር መዘጋጀቱ በዓሉን ልዩ ያደርገዋል።




የኤክስፖው ተሳታፊዎች ይዘው ከቀረቧቸው መካከል የኦሮሞ ብሔረሰብ ባሕላዊ አልባሳት ይጠቀሳሉ።

በዓሉ በዚህ መልክ እንዲከበር መደረጉ አንዱ ከሌላው ብዙ እንዲማርና የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ ኢኮኖሚያዊ አበርክቶው ጉልህ ነው የምትለው ወይዘሮ ፀሐይ፤ እሬቻ በኦሮሞ ብሔረሰብ በድምቀት የሚከበር የምስጋና በዓል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከባሕላዊ ምግቡ በተጨማሪ ወጣቶች በተለያዩ ጌጣጌጦች እንደሚያሸበርቁ ገልጻለች። ወቅቱ ባሕልን ለማስተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን በመጥቀስም ቀጣይነት ባለው መልኩ በዓሉን ማስተዋወቅና ወደ ቢዝነስ መቀየር እንደሚያስፈልግ አመላክታለች፡፡

ወይዘሮ ፀሐይ እንዳብራራችው፤ በኢሬቻ ኤክስፖው ላይ የተለያዩ የኦሮሞ ብሔረሰብ ባሕላዊ ምግቦች፣ ቁሳቁስ፣ አልባሳትና ጌጣጌጦች የቀረቡ ሲሆን፤ ነጋ የኦሮሞ ባሕላዊ ምግብም ባሕላዊ የሆኑ ምግቦችን ይዞ ቀርቧል። የኦሮሞ ባሕላዊ ምግቦች በአብዛኛው ከገብስና ከቀይ ጤፍ የሚዘጋጁ ናቸው። ጨጨብሳና ጮሮርሳ ከቀይ ጤፍ የሚዘጋጁ ናቸው፤ ጮሮርሳ በእርጎና በአይብ የሚበላ ምግብ ነው። ከገብስ የሚዘጋጀው ቆሪና ጨኮ የተባለው ባሕላዊ ምግብ በዋናነት በቅቤና ቅመማቅመም ታሽቶ ይዘጋጃል፡፡

እነዚህ የባሕል ምግቦች በማንኛውም ጊዜ ማህበረሰቡ የሚጠቀማቸው ቢሆኑም በተለየ ሁኔታ የሚዘጋጁት ግን ለእንግዳ፣ ለአራስና ለዘመድ ጥየቃ ነው። እነዚህን ልዩ ጣዕም ያላቸውን ባሕላዊ ምግቦች ከተማ ላለው ነዋሪ ተደራሽ ለማድረግ ማዘጋጀቱን በመኖሪያ አካባቢያቸው ቡራዩ አካባቢ እንደጀመሩት ያነሳችው ወይዘሮ ፀሐይ፤ ሰው በጣም እንደሚፈልጋቸውም ገልጻለች።

በተለያዩ ምክንያቶች ምግቦቹን በስፋት መሥራት ባይቻልም፣ ሰው በሰው በመጠቀም ገበያ ውስጥ መግባት እንደቻሉም ትናገራለች። በቀጣይም አስፍተው ለመሥራት ማቀዳቸውን ጠቅሳ፣ ለዚህም ኤክስፖው ላይ መሳተፋቸው ከበርካቶች ጋር ሊያስተዋውቃቸው እንደሚችል ተናግራለች። በአሁኑ ወቅት ከሀገር ውስጥ ባለፈ በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባሕላዊ ምግቦቹን በትዕዛዝ እንደሚያሰሩና እስካሁን ካናዳ፣ አሜሪካና ኖርዌይ መላክ እንደቻሉም ገልጻለች፡፡

እሬቻ ማለት ከክረምቱ ጨለማ ብራ ወደ ሆነው መስከረም መሸጋገርን የሚያሳይና ይህን የጨለማ ጊዜ በመሻገሩ የኦሮሞ ሕዝብ በአንድነት ሆኖ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት በዓል ነው ስትል ያብራራችው ወይዘሮ ፀሐይ፤ የአንድነትና የምስጋና በዓል የሆነው እሬቻ በሰላምና በድምቀት መከበር እንዳለበትም አስታውቃለች። በዓሉን ለሚያከብሩና ለሀገሪቱም ሰላምና መልካሙን ተመኝታለች።

የአዳማው ፊራኦል ዲዛይንም በእሬቻ ኤክስፖው ላይ የኦሮሞ ባሕላዊ አልባሳትን ይዞ ቀርቧል። በፊራኦል ዲዛይን የተለያዩ የኦሮሞ ባሕላዊ አልባሳት እንደሚዘጋጁ የጠቀሰችው ወጣት ሳምራዊት በቀለ የድርጅቱ የሽያጭ ባለሙያ ናት። እሬቻ ኤክስፖ 2017 ለመጀመሪያ ጊዜ መዘጋጀቱን ጠቅሳ፣ ኤክስፖው መጀመሩን ጥሩ ብለዋለች። በቀጣይ እየሰፋና እየደመቀ እንደሚሄድ ዕምነቷ መሆኑንም ገልጻለች።

በኤግዚቢሽኑ የወንድ፣ የሴት፣ የአዋቂና የህጻናት የኦሮሞ ባሕልን የሚገልጹ ባሕላዊ አልባሳትን ይዘው መቅረባቸውን ወጣት ሳምራዊት ጠቅሳ፣ እንዲህ አይነቶቹ ባዛርና ኤግዚቢሽኖች የገበያ ትስስር ለመፍጠርና ልምድ ለመለዋወጥ ዕድል እንደሚሰጡም ተናግራለች። በተለይም በእሬቻ በዓል ላይ ሊለበሱ የሚገባቸው አልባሳትና ጌጣጌጦች በስፋት ወደ ገበያው እንደሚመጡ አስታወቃ፣ ይህም ባሕልን ከማስተዋወቅ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ሰፊ ነው ትላለች። ከበዓሉ ጋር ተያያዥ የሆኑ አልባሳት፣ ምግብና ጌጣጌጦችን በማዘጋጀት ቢዝነስ መሥራት የቻሉ በርካቶች መሆናቸውን ጠቅሳ፣ በቀጣይም ኤክስፖው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቃለች።

በኤግዚቢሽኑ ዝግጅት የተሳተፈው የሀገሬ ኢቨንት ምክትል ማናጀር አቶ ጥላሁን ጫላ እንዳሉት፤ የእሬቻ በዓል በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ የሚሳተፍበትና በባሕላዊ እሴቱ በስፋት የሚታወቅ በዓል ነው። ይህን ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን ለማጉላት ታስቦ የተዘጋጀ ኤክስፖ ነው። ኤክስፖውን የሚጎበኙ በርካታ ሰዎች በኤግዚቢሽኑ ባሕላዊ ምግቦቹን፣ አልባሳቱንና ጌጣጌጡን እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁስን ጭምር ማግኘትና በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንዲችሉ ተደርጓል፡፡

የእሬቻ በዓል የኦሮሞ ባሕልን ከማስተዋወቅ ባለፈ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ድርሻ ለመጠቀም ታስቦ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው እሬቻ ኤክስፖ 2017 በታሰበው ልክ የተሳካ ነው ማለት ይቻላል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ በኤግዚቢሽኑ የተለያዩ ባሕላዊ ምግቦችና አልባሳት እንዲሁም ጌጣጌጦችን የሚሰሩ ሰዎች ምርቶቻቸውን ይዘው ቀርበዋል። ሸማቹም እየጎበኘና እየሸመተ መሆኑን ተናግረዋል። በተለይም በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ የማይታወቁና ጥሩ የሆነ ጣዕም ያላቸው የኦሮሞ ባሕላዊ ምግቦችን በማስተዋወቅ ረገድ ሰፊ ድርሻ አለው ሲሉ ጠቅሰው፣ ከባሕላዊ አልባሳትና ምግቦች በተጨማሪ የተለያዩ የምግብ ሸቀጦችም መቅረባቸውን ተናግረዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በእሬቻ ኤክስፖው በ250 ሺ ጎብኚዎች እንደሚጎበኝ ተገምቷል። 100 የሚደርሱ ጥሪ የተደረገላቸው አቅራቢዎችም ምርቶቻቸውን ይዘው ቀርበውበታል። ባንኮችና ኢንሹራንሶች ተገኝተውበታል።

ኢግዚቢሽኑ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ በዚህ ዝግጅት ከዚህ በኋላ ሰዎች እሬቻን ሲያስቡ ኤግዚቢሽንና ባዛሩን ጭምር እንዲያስቡ ማድረግ ተችሏል ሲሉ አስታውቀዋል። ጎብኚዎች በኤግዚቢሽኑ የተመለከቷቸው የኦሮሞ ባሕላዊ ምግቦችን በስፋት ማድነቃቸውን አቶ ጥላሁን ገልጸዋል፡፡

በእሬቻ ኤክስፖ 2017 ተሳታፊዎች አብዛኞቹ ከአዲስ አበባ ከተማ የመጡ መሆናቸውን አመልክተው፣ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ያሉ ከተሞችም መሳተፋቸውን ተናግረዋል። ከአዳማ፣ ከሻሸመኔና ከሸገር ሲቲ የመጡ ስለመኖራቸው ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኤክስፖው ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀ በመሆኑ ተሳታፊዎችን በተፈለገው መጠን ማስገባት አልተቻለም። ከዚህ ትምህርት በመውሰድ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤ በዚህም በርካቶችን ተደራሽ ማድረግ የሚቻልበት ዕድል ይፈጠራል። ይህም ባሕሉን ከማስተዋወቅ ባለፈ ኢኮኖሚውን በማነቃቃት ረገድ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

‹‹እሬቻ ምስጋና የሚቀርብበት በዓል ነው፤ ኦሮሞ ክረምቱን የጨለማ ወቅት አድርጎ የሚያይ በመሆኑ መስከረም ሲጠባ ከጨለማው ዘመን ወደ ብርሃናማ ዘመን በሰላም ያሸጋገርከን ፈጣሪ እናመሰግንሃለን በማለት አምላኩን አብዝቶ የሚያመሰግንበት በዓል ነው›› ብለዋል። በእሬቻ በዓል በስፋት የሚንጸባረቀው ባሕላዊ እሴቱ መሆኑን ጠቅሰው፣ ማንኛውም ሰው ወደ ኤግዚቢሽኑ በመምጣት የኦሮሞን ባሕል፣ እምነትና እሴቱን መማርና መረዳት ይችላል ብለዋል።

ከመስከረም 18 ቀን እስከ 24 ቀን 2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል የሚካሄደው "እሬቻ ኤክስፖ 2017" የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳተፍ፣ በውጭ ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ታዳሚ የሚሆኑበት መሆኑ ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ደራራ ቱለማ ኤክስፖው በሚቀጥሉት ዓመታት በቋሚነት እንደሚዘጋጅ አመልክተዋል። እሬቻ ታላቅ የምስጋና በዓል እንደመሆኑ፤ ኤክስፖውም ይህንኑ ያሳያል ብለዋል። ባሕላዊ ኤግዚቢሽኖች እና ትርኢቶች የእደ ጥበብ ወርክሾፖች፣ አገልግሎትና ምርቶች የሚቀርቡበት ባዛር መሆኑን አብራርተው፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ ክፍለ ጊዜዎችን በማካተት ጭምር በርካታ ተግባራት የሚቀርብበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ባሕሉን ከማስተዋወቅ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው አስታውቀዋል።

የኦሮሞ አባገዳዎች ህብረት የእሬቻ በዓል አከባበርን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፣ በዓሉ መስከረም 25 ቀን ሆራ ፊንፊኔ በአዲስ አበባና መስከረም 26 ቀን በቢሾፍቱ ሆራ ሀርሰዴ ይከበራል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የማን ጀርባ ይጠናል?

**ዋሰልኝ አየለ**

በዘመነ ኢህአዴግ ይቺ ቃል በጣም ታዋቂ ነበረች። በቀልዱም በቁም ነገሩም «ጀርባው ይጠና» የሚለው ቃል በተደጋጋሚ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር። ቀልዶች የተፈጠሩት የየተቋማቱ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በውሃ ቀጠነ ምክንያት ሁሉ የዓይኑ ቀለም ያላማራቸውን ሠራተኛ ወይም ኃላፊ «ጀርባው ይጠና» ይሉ ስለነበር ነው። የተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ይህን ንግግር የወረሱት የበላይ አለቆቻቸው በጋዜጣና መጽሔት ሥርዓቱን ይሞግቱ የነበሩ ሰዎችን «ጀርባው ይጠና» ሲሉ ይሰሙ ስለነበር ነው።

የፖለቲካ ባህላችን አሁንም አልተሻሻለም። በአሁኑ ወቅት ደግሞ በሰፊው የምንታዘበው ህፀፅን መናገርን አለመውደድ ነው። እርግጥ ነው ሁሌ ችግርን ብቻ መናገር ጤነኝነት አይደለም፤ የሚደነቁ ነገሮችን በሚገባ አድንቀናል። ዳሩ ግን የሚታዩ ችግሮችን የሚናገርን ሁሉ እንደ ጨለምተኛ ማየትም ጤነኝነት አይደለም፤ ሰዎች ቢያንስ ተናግረው ሊወጣላቸው ይገባል፡፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንድ የሚገርመኝ ነገር «ጀርባው ይጠና» የሚባለው ነገር ነው። ድሮም ሆነ ዛሬ ጀርባ አጥኚዎች የማን ጀርባ መጠናት እንዳለበት አያውቁም። ብዙ ጊዜ «ጀርባው ይጠና» ሲባል የምንሰማው በግልጽ እና በድፍረት የሚናገርን ሰው ነው። በግልጽ እና በድፍረት የሚናገር ሰው እኮ ምንም የሚጠና ጀርባ የለውም። በማህበረሰባችን አባባል እንዲህ አይነት ሰው «የግንባር ሥጋ» ይባላል። ፊት ለፊት የሚታይ ማለት ነው፤ ነገሩ ሁሉ ግልጽ የሆነ ማለት ነው። ስለዚህ በግልጽ እና በድፍረት የሚናገርን ሰው፤ የተናገረው ነገር ትክክል አለመሆኑን መንገር እንጂ የሚጠና ጀርባ የለውም። የተናገረው ነገር የማይጠቅም መሆኑን መንገር፣ የማያዋጣና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን መንገር እንጂ «ጀርባህ ይጠና» ማለት አጉል ፍርሃት ነው።

«የአገሌ ተላላኪ!» የሚል ስም መለጠፍ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ኋላቀር የፖለቲካ ባህላችን ነው። የጥፋት ኃይሎች ተላላኪ የሆነ ሰው እኮ እየተንጨረጨረ አይደለም የሚናገረው። የጥፋት ኃይሎችን የጥፋት ዓላማ የያዘ ሰው ተመሳስሎና ሳያስነቃ ነው እንጂ ሥራውን የሚሠራ በግልጽ እየተናገረ አይደለም። በአሠራሮች እየተቆረቆረ «ይህ ይስተካከል» ሊል አይችልም። ብልሹ አሠራሮችን እየሞገተ ስውር ተልዕኮ ሊይዝ አይችልም።

ከዚህ ይልቅ መንግሥት ብልጥ ከሆነ ማጥናት ያለበት ከልክ በላይ የሚያሽቃብጡ የሥራ ኃላፊዎችንና ባለሥልጣናትን ጀርባ ነው። ሆዳቸው የማይታወቅ ሰዎችን ነው።

በነገራችን ላይ አንድ ሀቅ እንተማመን። አብዛኛው የመንግሥት የሥራ ኃላፊ ራሱን የሚሸውድ ነው። በሚያወራው ነገር አያምንበትም። እስኪ ማን ይሙት የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንን በቋሚነት ይከታተላሉ? ከቤታቸው ቢገባ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ተከፍቶ ይገኛል? ጠረጴዛቸው ላይ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ይገኛል? ልጆቻቸው የመንግሥት ትምህርት ቤት ይማራሉ? ዓላማቸውና የረጅም ጊዜ ዕቅዳቸው ከሀገር ውጭ መሆኑን አናውቅም?

ለዚህም ነው አንድ በመንግሥት ተቋም ውስጥ ከሠራተኝነት እስከ ከፍተኛ ኃላፊነት ወይም በመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣንነት የቆዩ ሰዎች ከሀገር ከወጡ በኋላ ሲያገለግሉት የነበረውን ተቋም ወይም መንግሥት የሚራገሙት። ጀግና ከሆኑ እነዚያን ችግሮች መናገር የነበረባቸው ባለቡት የሥራ መደብ ወይም ኃላፊነት ላይ ሆነው ነው። አለበለዚያ ራሳቸውን እየሸወዱ ነበር ማለት ነው። ራሳቸውን እየዋሹ ነበር ማለት ነው። እየኖሩ የነበረው የማያምኑበትን ነበር ማለት ነው። አሁንማ እንዲያውም ጭራሽ ባህል ተደርጎ «እና የመንግሥት ቤት ሆኜ ይሄን ልናገርልህ ነው?» ይላሉ። አስመስሎና ራስን ሸውዶ መኖር ባህል ሆነ ማለት ነው?

ጋዜጠኛና ደራሲ በረከት በላይነህ ከወራት በፊት በአንድ ፖድካስት ላይ ቀርቦ፤ የመንግሥት ተቋም ውስጥ ገብቶ በኃላፊነት መሥራት እንደሚፈልግ ሲናገር፤ ጠያቂው «የመንግሥት ቤት ውስጥ የምትፈልገው ነፃነት አለ ወይ?» ብሎ ጠየቀው። ጠያቂው ሲባል ከሚሰማው ነገር ተነስቶ ይህን ጥያቄ መጠየቁ ትክክል ነው። የበረከት መልስ ግን ብዙዎችን አስገርሞ ነበር።

የበረከት መልስ ሲጠቃለል፤ አንዳንድ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ከልክ በላይ የሚያሸረግዱት መንግሥት በዚያ ልክ ሁኑልኝ እያላቸው አይደለም። በራሳቸው እውደድ ባይነት ባህሪ ነው። በዚያ ልክ መሆን ግዴታ አይደለም ብሎ ያምናል ማለት ነው በረከት በላይነህ፡፡

በእርግጥ እዚህ ላይ አከራካሪ ነገር ይነሳል። መንግሥት ሲባል እስከ የት ድረስ ያለው ነው? የሚለው ያከራክራል። ምክንያቱም ከጥበቃና የጽዳት ሥራ ጀምሮ የመንግሥት አካል ነው። በልማድ ግን መንግሥት የምንለው በዋናነት የሀገሪቱን መሪ እና ሌሎች በከፍተኛ ባለሥልጣን ላይ ያሉትን ነው። እነዚህ አካላት የበታች አመራሮችንና የየተቋማቱን የሥራ ኃላፊዎች በዚያ ልክ እንዲሆኑላቸው ያዝዟቸው አያዝዟቸው ማወቅ አይቻልም። ምናልባት ራሳቸውም ከፍተኛ አመራሮች ወደውት ካልሆነ በስተቀር «በዚህ ልክ አትሁኑ» ብለው መምከር ይችሉ ነበር።

ወደ ጀርባ ጥናት እንመለስ።

ብዙ ጊዜ የውጭ ሀገር ዕድል ተሰጥቷቸው ወይም ለሥራ ተልከው ሀገራቸውን ከድተው የሚቀሩት ጋዜጠኞችም ሆኑ ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ከልክ በላይ ታማኝ የነበሩ ናቸው። የኮምፒውተራቸውን እና የስልካቸውን ስክሪን ሽፋን የየወቅቱን የሀገሪቱን መሪ ምስል የሚያደርጉ ናቸው። በየንግግሮቻቸው ሁሉ የየወቅቱን መሪ ንግግሮች እያጣቀሱ የሚያወድሱ ናቸው። መጠናት ያለበት የእነዚህ ሰዎች ጀርባ ነው። እነዚህ ሰዎች ዕድሉን ቢያገኙ ሀገራቸውንም ተቋማቸውንም ከመክዳት አይመለሱም። ብዙዎችን አይተናል። ጥገኝነት ለመጠየቅ የሀገራቸውን ችግር መናገር ሲበቃቸው የግለሰቦችን ገመና ሁሉ እያወጡ የሚያብጠለጥሉ ናቸው። ዕድልና አጋጣሚ የሚጠብቁ አስመሳዮች ነበሩ ማለት ነው።

ብልሹ አሠራሮችን በግልጽ እና በድፍረት የሚናገሩ ሰዎች ግን ተቆርቋሪዎች ናቸው። «ምን አገባኝ!» በማለት ሀገርና ተቋምን ለመክዳት ዕድልና አጋጣሚ የሚጠብቁ አይደሉም። የተቋማቸውም ሆነ የሀገራቸው ጉዳይ ያገባቸዋል፤ የሚንጨረጨሩትና በብሶት የሚናገሩትም ስለሚያገባቸውና ስለሚቆረቆሩ ነው። እንደማንኛውም ሰው «ምን አገባኝ!» ማለት ይችሉ ነበር። በኃላፊነት ላይም ሆነ በተራ ሠራተኝነት ላይ ሆኖ «ምን አገባኝ!» ማለት ገለልተኝነት ሳይሆን እልም ያለ ስንፍና ነው።

በእርግጥ የመንግሥት ፍርሃትም ይገባኛል። ብልሹ አሠራሮችን የሚናገሩ ሰዎች ሌሎች ሠራተኞችንም ያነቃቃሉ፤ ወቀሳ ይበዛብኛል ከሚል ፍርሃት ነው። ይህ ግን ራስን መሸወድ ነው። ሰዎች ጤነኛ የሚሆኑት ተናግረው ሲወጣላቸው ነው። አለበለዚያ አለቃ ፊት እየተልመጠመጡ በየኮሪደሩ ግን በሀሜትም ቢሆን መውቀሳቸው አይቀርም። በነገሥታቱ ዘመን «እረኛ ምን አለ?» ይባል ነበር አሉ። በአደባባይ የተከለከለ ሕዝብ በእሳት ዳር ጨዋታ መንግሥትን ስለሚያማርር ማለት ነው። በአደባባይ በግልጽ የሚናገር ሰው ግን ሹክሹክታ አይወድም። ተናግሮ ጨረሰ፣ ጆሮ ጠቢ ሰማኝ አልሰማኝ ግራ ቀኙን እያየ ሀሜት አያበዛም። አድርባይና ፈሪ ግን ተጠራጣሪ ይሆናል፤ በዙሪያው ያለ ሰው ሁሉ ሰላይ እየመሰለው በራስ መተማመን ያጣል።

ከፍተኛ አመራሮችም ሆኑ ተራ ሠራተኞች ብግልጽ እንድናገሩ ካልተደረገ፣ በሆነ አጋጣሚ ከሀገር ሲወጡ ያላዩትንና ያላጋጠማቸውን ሁሉ እየጨማመሩ ያወራሉ ማለት ነው። ስለዚህ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችም ነፃ ውይይቶችን ይፍቀዱ፣ ያመቻቹ። የማን ጀርባ መጠናት እንዳለበትም ልብ ይበሉ!

# ዓለም አቀፍ



## የየመኑ ሃውቲ የናስራላህ ግድያን ተከትሎ መሪዎቹን ወደ ሳዳ ዋሻ ማዛወሩ ተነገረ

የሄዝቦላህ መሪ ሀሰን ናስራላህ በእስራኤል መገደል የየመኑ ሃውቲ ቡድን መሪዎቹን ለመጠበቅ የተጠናከረ ርምጃ እንዲወስድ አድርጎታል ተባለ። ወታደራዊና የደህንነት ምንጮች እንደገለጹት፥ የየመኑ ቡድን ዋና ዋና መሪዎቹ በእስራኤል የግድያ ኢላማ ውስጥ እንዳይገቡ ሙሉ በሙሉ ከሕዝብ እይታ እንዲሰወሩ አድርጓል።ሃ ውቲዎች የሄዝቦላህ እና ኢራን አማካሪ ባለሙያዎችን ለደህንነታቸው የተሻለ ነው ወደተባለው የሳዳ ዋሻ ማዛወራቸውንም ነው ምንጮቹ ያነሱት።

ቡድኑ በሳዳ አስቀድሞ ተዘጋጅቶበት ለሥራ አመቺ አድርጎ የሠራው ዋሻ ወታደራዊ ቁሳቁሶች የተሟሉለትና የአደጋ ጊዜ ወታደራዊ ማዘዣ ሆኖ ሲያገለግል መቆየቱም ተገልጿል። አካባቢው በበርካታ ተራራዎች የተከበበ መሆኑም በእስራኤል የአየር ጥቃት ኢላማ የመደረግ እድሉን ያጠበዋል ተብሎ ታምኖበታል።

በአሜሪካ መረጃ አቀባይነት የሃውቲ መሪዎች እንዳይገደሉ በሚልም ቡድኑ በዓለምአቀፍ ድርጅት ተቀጥረው በመሥራት ለዋሽንግተን ሲሰልሉ ነበሩ የተባሉ የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ቤተሰቦችን በቁጥጥር ስር ማዋሉም ተሰምቷል። የየመኑ ሃውቲ በመዲናዋ ሰንአ ለአደጋ ጊዜ መደበቂያ የሚሆኑ ዋሻዎች መገንባታቸውንና የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮችም ከሀምሌ ወር ጀምሮ በነዚህ ዋሻዎች ውስጥ እንዲገቡ መደረጉን አል ዐይን ዘግቧል።

## በሩዋንዳ በማርበርግ ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ሲጨምር ዘጠኝ ሰዎች ሞቱ



በሩዋንዳ በማርበርግ በተባለው ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ቁጥር 27 የደረሰ ሲሆን፣ ዘጠኝ ሰዎች በቫይረሱ ሳቢያ ሕይወታቸው ማለፉን የሀገሪቱ ባለሥልጣናት አስታወቁ። የሩዋንዳ የጤና ባለሥልጣናት እንደተናገሩት፣ በአሁኑ ወቅት በቫይረሱ የተያዙ 18 ሰዎች ለይቶ ማቆያ ውስጥ ሕክምና እያገኙ ነው።

ማርበርግ ቫይረስ በሩዋንዳ መገኘቱ ከተረጋገጠ ሳምንት ሆኖታል። ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲደረግ ማሳሰቢያም ተላልፏል። የዓለም ጤና ድርጅት የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት እና ለቫይረሱ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን ለመጠበቅ ከሩዋንዳ ጋር በትብብር እየሠራ ነው። መመርመሪያ መሣሪያ፣ የጤና ባለሙያዎች የጥንቃቄ አልባሳት እና ቁሳቁስ እንዲሁም እስከ 500 ሰዎች ማከም የሚያስችሉ መሣሪያዎችን ድርጅቱ ለግሷል።

በቫይረሱ የመያዝ ምልክት ካሳዩ ሰዎች ጋር ንክኪ ከማድረግ መቆጠብ እንደሚያስፈልግም ለሕዝቡ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል። የሩዋንዳ ጤና ሚኒስትር የህመሙ ምልክቶች ራስ ምታት፣ በላብ መጠመቅ፣ የጡንቻ ህመም፣ ማስመለስ እና ማስቀመጥ ናቸው ብሏል። ከፍተኛ የደም መፍሰስ ቫይረሱ ስለሚያስከትል ለሞት ይዳርጋል።

በቫይረሱ ተይዘው ሆስፒታል የገቡ ሰዎች ለ14 ቀናት ማንም እንዳይጠጋቸው ይደረጋል። የሩዋንዳ የጤና ሚኒስቴር እንዳለው አብዛኞቹ በቫይረሱ የተያዙት የሕክምና ባለሙያዎች ናቸው። የሩዋንዳ ጎረቤት ሀገር ብሩንዲም የሕክምና ማዕከል ማዘጋጀትን ጨምሮ የጥንቃቄ ርምጃዎችን እየወሰደች ነው።

ብሩንዲ አሁን ላይ ከዝንጀሮ ፈንጣጣ ጋርም ትግል ላይ ትገኛለች። 400 በቫይረሱ እንደተያዙ የተጠረጠሩ ሰዎች አሉ። እስካሁን ግን ሞት አልተመዘገበም። በሩዋንዳ በማርቡርግ ቫይረስ የሞቱ ሰዎች የቀብር ሥነ ሥርዓት በ50 ሰዎች ብቻ እንዲከናወን መመሪያ ወጥቷል። የቫይረሱ የመግደል አቅም 88 በመቶ ሲሆን፣ ከኢቦላ ጋር ተመሳሳይ የተዋህሲ ቤተሰብ ውስጥ ይገኛሉ።

ከሌሊት ወፍ ወደ ሰዎች ቫይረሱ ይተላለፋል። በሰውነት ፈሳሽ ንክኪ ከሰው ወደ ሰው ይሻገራል። በቦስተን ዩኒቨርሲቲ ማዕከል የተላላፊ በሽታዎች ተመራማሪ ዶ/ር ናሂድ ባዲሊያ እንዳለችው፣ አብዛኞቹ ሕሙማን በተጨናነቁ የኪጋሊ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ስለሆኑ የቫይረሱን ስርጭት ለመግታት አስቸጋሪ ይሆናል።

በሩዋንዳ ካለው ጠንካራ የኀብረተሰብ ጤና መሠረተ ልማት አንጻር ግን የከፋ ላይሆን እንደሚችል አክላለች። ዜጎች እጅ መታጠብን ጨምሮ የግል ንጽህና እንዲጠብቁ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል። በቫይረሱ ከተያዙ ሰዎች ጋር ንክኪ ያላቸው 300 ሰዎች ክትትል እየተደረገባቸው ነው። እአአ በ2023 በታንዛንያ ቫይረሱ ተነስቶ የነበረ ሲሆን በኡጋንዳ ሦስት ሰዎች ሞተዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ

# አዲስ አበባ የዓለም ሦስተኛ የዲፕሎማሲ ማዕከል. . .

**ከ5ኛ ገፅ የዞረ**

እነዚህ የልማት ሥራዎች የከተማዋን ጎስቋላ ገፅታ በሚፈለገው አግባብ እየለወጡ ያሉ፤ ከወትሮ በተሻለ ሰፋፊ የሥራ ዕድሎችን የፈጠሩ፤ ወሳኝ የመንግሥት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ያሳለጡ ከመሆናቸውም ባሻገር የከተማዋን ገቢ ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋገሩ ስለመሆናቸውም ከንቲባ አዳነች ካለፉት ጊዜያት ጋር በማነጻጸርም ጭምር በከተማው ምክር ቤትና በተለያዩ መድረኮች ላይ ተናግረዋል።

በከተማዋ አዲስና እየዳበረ ያለውን አሁናዊ የፕሮጀክቶች የሥራ አፈጻጸምን በማስመልከት፤ ከንቲባዋ ለከተማው ምክር ቤት በተደጋጋሚ የሰጧቸውን ማብራሪያዎች በመንተራስ ያስገኟቸውን ውጤቶች በቀናነት በመመልከት ብቻ ከተማዋ፤ በሁሉን አቀፍ የለውጥ ሂደት ላይ መሆኗን በልኩ መረዳትና ማድነቅ እንዲሁም መደገፍ ለሚፈልግ አካል ሁሉ የሚቻል እንጂ አሻሚ የሚሆን አይሆንም። ይህንኑ ጀምሮ የመጨረስ አዲስና እየዳበረ የመጣውን የፕሮጀክት አመራር ልምድ ተከትሎ፤ ከንቲባ አዳነች የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራምን ጨምሮ በየዘርፉ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና ሀገራት ልዩ ልዩ የማበረታቻ ሽልማቶችን መቀበላቸውም ይታወቃል።

ከለውጡ ማግስት አንስቶ በተከታታይ በፕሮጀክቶች አመራርና አስተዳደር ረገድ በተጨባጭ የታየው ስኬትና ውጤት ሊመዘገብ የቻለው መንግሥት የመፈፀም አቅሙን በማሳደጉ፤ ብክነትን መቀነስ መቻሉን ጨምሮ የልማት አጋሮችን እና የነዋሪውን ሁለንተናዊ አቅም አስተባብሮ መጠቀም በመቻሉ የተገኘ ስለመሆኑ ከንቲባዋ ለከተማው ምክር ቤት የ2016 የሥራ አፈጻጸምን በማስመልከት በሰጡት ማብራሪያ ወቅት ተናግረዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአዲስ አበባ ከተማን ዓለም አቀፍ ተቀባይነትና የነዋሪዎቿን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በሚፈለገው ልክና አግባብ እንደሚያሻሽል ታምኖበት በከተማዋ ተጀምሮ የነበረው የኮሪደር ልማት ሥራ፤ ሁለተኛውን ምዕራፍ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር በቅርቡ በይፋ አስጀምረዋል። በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት የማስጀመሪያ መርሀ-ግብር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራና በቅንጅት ለተገኘው ስኬት ለከተማዋ አመራሮች የማበረታቻ ዕውቅናና ሽልማት መስጠታቸውም እንዲሁ የሚታወስ ነው።

24/7 አስቀድመው በጥናት በተለዩ አምስት የኮሪደር ልማት መዳረሻዎች በጥብቅ የአመራር ዲስፕሊን ሲከናወን የነበረው፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳና ጥራት ተጠናቆ ለሕዝባዊ አገልግሎት ክፍት መደረጉ በየመዳረሻቸው ምርቃት ወቅት ይፋ ተደርጓልም።

በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ሃሳብ አመንጪነት ፤ የመጀመሪያው ምዕራፍ የከተማዋ የኮሪደር ልማት ሥራ በአዋጪነት ጥናት ተረጋግጦ አንድ ተብሎ መጀመሩ የተነገረው። በተገባደደው የ2016 በጀት ዓመት በከተማዋ ተግባራዊ የተደረገው የኮሪደር ልማት ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ ፤ በከተማ ልማት ባለሙያዎች በኩል አስቀድሞ የተደረገው የአዋጪነት ጥናት አካታች ልማት ፣ በሁሉም ረገድ የሚገለጽ ዘላቂ ዕድገትና የነዋሪውን አዳጊ ፍላጎቶች ማዕከል ባደረገ አኳኋን የልማት ዕቅዶቹን ደረጃ በደረጃ መተግበር እንደሚገባም ነው በሪፖርታቸው ላይ በአጽንኦት የተጠቆመው። አተገባበሩም ይህንኑ የተከተለ እንዲሆን ከንቲባዋን ጨምሮ በየደረጃው በሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች ምሽቱን የሚያደርጓቸውን ጉብኝትና ክትትሎች በከተማዋ ማየት የተለመደ ነው።

የከተማዋ የኮሪደር ልማት ትግበራ፤ የጎረቤት ሩዋንዳ ኪጋሊ ከተማን ጨምሮ የሌሎችንም ዓለም አቀፍ ከተሞች ተሞክሮዎችን ዋቢ አድርጎ እንዲፈጸም ከመሆኑም ባሻገር፤ ከከተማዋ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባም በከተማ ልማት ባለሙያዎች ጥናት ወቅት ተጠቁሟል። ከተማ አስተዳደሩ የኮሪደር ልማት በሚያልፍባቸው መዳረሻዎች በባለሙያዎቹ ምክረ-ሃሳብ መሠረት ካሳ ተለዋጭ ቦታና በየደረጃው የሚገኙ ቤቶችን አስቀድሞ እያቀረበ ያለ ስለመሆኑ የልማቱ ተነሺዎች በተለያዩ ጊዜያት ለሚዲያ አካላት ከሰጧቸው ምስክርነቶች

> **በተለይም በኮሪደር ልማት ፕሮግራም ከሶስት እስከ አራት ወራት ባለው የተፈጸመው ግን የከተማችንን አጠቃላይ ገፅታ የቀየረ፣ አዲስ የሥራ ባሕልን ያዳበረ እና ለከተማችን ነዋሪዎች ምቹ መኖሪያ ከባቢን የፈጠረ ቅንጅታዊ የከተማ ልማት ሥራ እንደመሆኑ ከውስጥም ከውጪም የበርካቶችን ዕውቅና ያስገኘ ነውም ብለዋል**

መረዳት የሚቻል ይሆናል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ አጠቃላይ ግንባታቸው ተጠናቆ ለሕዝባዊ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ክፍት ተደርገው ከነበሩት አምስቱም የኮሪደር ልማት መዳረሻዎች መካከል ከአራት ኪሎ በመስቀል አደባባይ አድርጎ እስከ ቦሌ ድልድይ (7 ኪ.ሜትር)፤- ከቦሌ አየር መንገድ እስከ መገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ (4.9 ኪ.ሜትር)፤- ከመገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ በአራት ኪሎ አድርጎ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ድረስ (6.4 ኪ.ሜትር)፤ ከፒያሳ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ዙሪያ፣ በለገሃር ሜክሲኮ፣ በሳርቤት አድርጎ እስከ ወሎ ሰፈር (10 ኪ.ሜትር) ባለው የተከናወነው የልማት ሥራ በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው፡፡

በአምስቱም የኮሪደር ልማት መዳረሻዎች፤ ከ240 ኪ.ሜ በላይ መንገድ እና በተጓዳኝ በፕሮግራም ማዕቀፉ ተካተው የተከናወኑ መሰል መሰረተ ልማቶችን ጨምሮ 70 የከተማዋን የውስጥ ውበት ከመልካም የአየር ንብረት ጠባይ ጋር አዳምረው መንፈስን የማደስ አቅም ያላቸው የሕዝብ መናፈሻዎች ተገንብተው የከተማዋ ነዋሪ ከቤተሰቡ ጋር ባመቸው ሰዓት ሁሉ እየተገለገለባቸው መሆኑ ይታያል፡፡

ከተማዋን በሁሉም ረገድ ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ለማስቻል የተያዘውን ራዕይ ከማሳካት አኳያ፤ የከተማዋን ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ወደ ላቀ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚረዱ የፍሳሽ ማስተላለፊያዎች፣ በዓይነታቸው ልዩ የከተማዋን ሰላማዊነት የሚያፀኑ የደህንነት ካሜራዎች፣ የብልህ ትራንስፖርት ሥርዓት (intelligent transport system) በመሬት ውስጥ የመዘርጋት ሥራ ፣ ከ400 የሚልቁ ህንጻዎች ዕድሳትን ጨምሮ ወጥ የቀለምና የመብራት ሥራዎች እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት ዘመን ተሻጋሪ አገልግሎት እንዲሰጡ ሆነው በላቀ ጥራት እየተሰሩ ስለመሆናቸው ከተማ አስተዳደሩ የሚያወጣቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ከከተማ አስተዳደሩ እንደተገኘው መረጃ በመጀመሪያው ምዕራፍ፤ ለኮሪደር ልማት ፕሮግራም ተነሺዎች 6.2 ቢሊየን ብር ካሳ ለመክፈል የተቻለም ሲሆን ፤ ለልማቱ ተነሺዎች በተቀላጠፈ አኳኋን ለ2,538 ቦታዎች (33.4ሄ/ር) ምትክ መሬት በከተማው የመሬት ልማት ማኔጅመት ቢሮ በኩል ማስተላለፍ ተችሏም ተብሏል። በሌላ መልኩ የልማት ሥራው ለከተማዋ ነዋሪዎች ይዞት በመጣው መልካም ዕድል ሳቢያ፤ እጅግ ጎስቁለው ለመኖር አመቺ ያልሆኑ መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ በንግድ ቤቶች ውስጥ የነበሩ በርካታ የልማት ተነሺዎች ምቹ የመኖሪያ እና መሥሪያ ቦታ እንዲያገኙም አስቀድሞ ተደርጓል፡፡

በአገልግሎትና በአቅርቦት ሥራ ላይ የተሰማሩ ብዙሃን የንግዱ ማህበረሰብ አካላት፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በልማቱ ሳቢያ የተፈጠረው ሰፊ የገበያ ትስስር አካል በመደረጋቸው ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና ተጠቃሚነትን በከተማዋ እንዲረጋገጥ እያስቻለ የሚገኝ የልማት ሥራም መሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያሻው በፍሬው የሚታይ ነው።

ከሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት መጀመር አስቀድሞ፤ በቅርቡ ተመርቆ ለሕዝባዊ አገልግሎት ክፍት የተደረገው የአፍሪካ፣ የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ መግቢያ በር ተደርጎ የሚታየው የቦሌ መንገዶች የልማት ኮሪደር ፕሮግራም ርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ የንግድ፣ የቱሪዝም፣ የዓለም አቀፍ ኮንፈረንስና የልዩ ልዩ የስማርት ሲቲ አገልግሎቶች ማዕከል በተጨባጭ እየሆነች መምጣቷን ያረጋገጠም ሥራ መሆኑ በበርካቶች በምርቃቱ ወቅት የተነገረ ጉዳይ ነው። የቦሌ መንገዶች ፣ የልማት ኮሪደር ሥራ ወደ ቦሌ ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ እና ወደ ሌሎችም የከተማዋ አካባቢዎች በትራንስፖርት የሚደረግን ጉዞ በእጅጉ የተቀላጠፈ እንዲሆን አስችሏል፡፡

በቦሌ መንገዶች የኮሪደር ልማት ፕሮግራም ማዕቀፍ የተገነቡ፤ ልዩ ልዩ የቢዝነስ ማዕከላት፣ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና ሱቆች የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን ቀልብ በእጅጉ መሳብ ችለዋል። በዚህም በአካባቢው የሚከናወኑ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የምሽቱን ክፍለ ጊዜ ጨምሮ፤ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መነቃቃት እንዲታይባቸው ከመሆኑም ባሻገር ፤ መጪው ጊዜ ለከተማዋ ብሩህ መሆኑን አመላካች ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ከቦሌ ድልድይ እስከ መስቀል አደባባይ ድረስ ባለው በቦሌ መንገዶች የልማት ኮሪደር ፕሮግራም የሚከተሉትን ዐበይት ክንውኖች የያዘ ነው። 4.3 ኪሎ ሜትር የመንገድ ልማት፤ 10 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገድ ግንባታ፤ 13.2 ኪሎ ሜትር የብስክሌት መንገድ ግንባታ ፤ 30,160 ካሬ ሜትር የግራናይት እና የአስፓልት ንጣፍ ሥራ፤ 30 የአውቶቡስ እና ታክሲ መቆሚያ አገልግሎት ፤ 10 የስማርት ፓርኪንግ አገልግሎት መስጫ ስፍራዎች ፤ ከ10 የሚልቁ አነስተኛ የሕዝብ መዝናኛ ፓርኮች እና ማረፊያ ፕላዛዎችን ጨምሮ ከ500 በላይ በመንገድ ዳር የሚገኙ ሕንፃዎች እና ቤቶችን እድሳት አካቶ በልዩ ጥራት የተፈጸመ ስለመሆኑ በምረቃቱ ወቅት በአጽንኦት ማብራሪያ ተሰጥቶበታልም፡፡

በምርጫ ወቅት፣ ለከተማው ነዋሪ በመንግሥት ደረጃ ቃል የተገቡ የልማት ሥራዎችን ሁሉ ደረጃ በደረጃ እንደሚያስፈጽሙ ፤ በቦሌ የኮሪደር ልማት መዳረሻ የምርቃት መርሀ-ግብር ላይ የተናገሩት ከንቲባ አዳነች ፤ በሁሉም ረገድ ርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ማሟላት እንድትችል ታስበው የሚከናወኑ የመሠረተ-ልማት ዝርጋታዎች በመጪውም ጊዜ በይበልጥ ተጠናክረው የሚቀጥሉ ስለመሆናቸው አንስተው ልክ እንደ ቀድሞው ሁሉ የብዙሃንን ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

“አርቆ ማሰብ ፤ ለየት አድርጎ ማቀድ እንዲሁም በመፍጠንና በመፍጠር መርህ ርዕሰ መዲናዋን አዲስ አበባንም ሆነ ኢትዮጵያን በሚገባና በሚፈለገው ልክ በሁሉም ረገድ ለመቀየር እንዲቻል እንደ አንድ ሰው ሆኖ በቅንጅት ተግቶ መሥራት እንደሚገባ፤ በኮሪደር ልማት መዳረሻዎች የምርቃት መርሀ-ግብር ላይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)በተደጋጋሚ በአጽኖት ሲናገሩ መደመጣቸው የሚታወስ ከመሆኑም ባሻገር፤ ሀገራቸውን በሚወዱ ዜጎች ሁሉ ዘንድ ቅቡልነት የሚኖረውም ነው፡፡

በኮሪደር ልማት መርሀ-ግብር በከተማዋ ተግባራዊ ከሚደረጉ ዝርዝር የልማት ሥራዎች መካከል የመንገድ ኮሪደር ልማት፤ የወንዝ ዳርቻዎች አዋሳኝ የተፋሰስ ልማት ፣ የብስክሌትና ሞተር አልባ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ልማት ፣ ዘመናዊ የትራንስፖርት ተርሚናሎች ግንባታ፣ አገናኝ የኮሪደር ልማት ድልድዮች፣ ማሳለጫዎችና የመጋቢ መንገዶች ልማት፤ የመንገድ ዳር የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች ፤ ፋውንቴይኖች እና የሕዝብ መናፈሻ ስፍራዎች፤ ወጥ የህንጻ ቀለምና የከተማ ማብራት፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ፓርኪንጎች፣ የመኪና መጫኛና ማውረጃ አገልግሎቶችን ጨምሮ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን አካቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ከመሆኑም ባሻገር በተጨባጭ የታየም ነው።

“ ከተሞች ለወደፊቱ ለዜጎቻችን ክብር የሞላበት የኑሮ ዘይቤን ለማጎናፀፍ የሚመቹ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ይኖርብናል። ከተሜነት በሁሉም ረገድ እየተስፋፋ የሚሄድ መሆኑ የሚታወቅ ነው። እኛም ዘላቂ እና ምቹ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የሚያሟሉ ከተሞችን በዘላቂነት ለመፍጠር ሁሉም መሳሪያዎች አሉንም” ሲሉ የተናገሩት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) በከተማዋ እንደ ቀድሞው ሁሉ በተመሳሳይ ተግባራዊ የሚደረገውን ሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ በኢፌዴሪ ቤተ መንግሥት ባስጀመሩበት ወቅት ነው።

በመርሀ-ግብሩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለከተማዋ አመራሮች እንዳስተላለፉት መልዕክት፤ የተደረገላችሁ ዕውቅና ሽልማት የተሻለ የከተማ ከባቢ ለመፍጠር ያሳያችሁትን ትጋት እና ጠንካራ ሥራ የሚያንፀባርቅና ለላቀ ሥራ እንድትነሳሱ ድርብ ኃላፊነት እንዳለባችሁ ለማሳሰብም ጭምር የተደረገ እንደመሆኑ አስቀድሞ የነበራችሁን ጥንካሬ ማላቅ ከሁላችሁም የሚጠበቅ ነውም ማለታቸው የሚታወቅ ነው። ከመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ ብዙ ትምህርቶችን ቀስመናል። አሁን ተግባራዊ ለምናደርገው ሁለተኛውን ምዕራፍ የኮርደር ልማት ባላሰለሰ የመሻሻል ሂደት እና የሥራ ሥነ ምግባር በቀደመው ያሳካነውን ተቀናጅተን ለማላቅ ተነስተናልም ብለዋል።

በርዕሰ መዲናዋ አስቀድመን የጀመርነውን ይህንን የሀገርን ሁለንተናዊ ገጽታ የማሻሻል መልካም ሥራ ፤ በመላ ሀገራችን ለማስፋፋት የምናደርገውን ጥረት በመደገፍ ተመሳሳይ ሥራ የጀመሩ አስራ አንድ ከንቲባዎች አብረውን ረዳት በመሆን ተቀናጅተው ይሰራሉም ብለዋል ጠቅላይ ሚንስትሩ። ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፡-በእርሶ ሃሳብ አመንጪነት እና ቀዳሚ መሪነት ከተማችን አዲስ አበባ እንደስሟ ውብ አበባ እንድትሆን ለማድረግ ከለውጡ ማግስት አንስቶ እስከ ኮሪደር ልማቱ ድረስ በርካታ የልማት ስኬቶችን በሁሉም ረገድ አስመዝግበናል።

በተለይም በኮሪደር ልማት ፕሮግራም ከሶስት እስከ አራት ወራት ባለው የተፈጸመው ግን የከተማችንን አጠቃላይ ገፅታ የቀየረ፣ አዲስ የሥራ ባሕልን ያዳበረ እና ለከተማችን ነዋሪዎች ምቹ መኖሪያ ከባቢን የፈጠረ ቅንጅታዊ የከተማ ልማት ሥራ እንደመሆኑ ከውስጥም ከውጪም የበርካቶችን ዕውቅና ያስገኘ ነውም ብለዋል። ይህ ዕውቅናና ሽልማት የከተማው አመራር ብቻ ያስገኘው ሳይሆን መላው የከተማችን ነዋሪዎች በተለይም በኮሪደር ልማት አካባቢ የሚገኙ ዜጎች ትብብርን ጨምሮ፣ ኮንትራክተሮችና ኮንሰልታንቶች እንዲሁም አብረውን በጋራ የመልካም ሃሳባችን ደጋፊ ሆነው ለቆሙ በሙሉ ማስታወሻ ሊሆን የሚገባ ነውም ሲሉ ከንቲባዋ መናገራቸውም ይታወሳል።

የአዲስ አበባ ከተማን ፣ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊ ተቀባይነትና የነዋሪዎቿን በሁሉም ረገድ የሚገልጽ አዳጊ ፍላጎቶች በሚፈለገው ልክና ፍጥነት ማረጋገጥ እንዲቻል ልክ እንደ ቀድሞው ሁሉ፤ የሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ 24/7 በከተማ አስተዳደሩ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በተዋረድ በሚተገበር ቅንጅታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ተፈጻሚ የሚደረግ መሆኑን በማስጀመሪያ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ከንቲባዋ አዳነች በአንክሮ አረጋግጠዋል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ ሕዝባችን በምርጫ 2013 በፀሐይ እና ዝናብ ውስጥ ሆኖ ፓርቲያችንን በመምረጥ የሰጠንን መንግሥታዊ ኃላፊነት ወደ አመርቂ ውጤት የምንለውጥበት ነው ያሉት የከተማዋ አመራሮች፤ 2017 የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት፤ ለአዲስ አበባ አዲስ የተስፋ ብርሃን ጮራ ይዞ መምጣቱን በመግለጽም ጭምር ሁለተኛውን ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ በላቀ ደረጃና ጥራት ጀምሮ ለመጨረስ የሚያስችል ዝግጅት አስቀድሞ በከተማዋ ሲደረግ የነበረ መሆኑንም አመልክተዋል።

# ስፖርት





# የትግራይ ክለቦች ተስፋ ሰጪ የፕሪሚየር ሊግ አጀማመር

ዓስማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የውድድር ዓመቱን ከጀመረ ሶስተኛ የውድድር ሳምንቱን ያስቆጠረ ሲሆን፣ ክለቦች በድሬዳዋ ከተማ ላይ ተሰባስበው ውድድራቸውን እያካሄዱ ይገኛሉ። አራት ዓመታት ከሊጉ ርቀው የቆዩት የትግራይ ክልል ክለቦችም በተመለሱበት ዓመት ጥሩ አጀማመር እያሳዩ ይገኛሉ፡፡

በ19 ክለቦች መካከል እንደሚካሄድ ታቅዶ መጀመሩ ይታወሳል። ወልቂጤ ከተማ ከክለብ ፍቃድ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ማሟላት የሚገባውን ሰነድ ባለማቅረቡ በኢትዮጵያ እግር ፌዴሬሽን የዲሲፕሊን መመሪያ መሠረት በአወዳዳሪው አካል ከሊጉ መሰረዙን ተከትሎ በ18 ክለቦች መካከል ለመካሄድ ተገዷል። በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ከሁሉም ውድድሮች ርቀው የተመለሱት የትግራይ ክልል ሶስት ክለቦች በፕሪሚየር ሊጉ አበረታች እና ተስፋ ሰጪ ጅምር አሳይተዋል፡፡

ክለቦቹ ለአራት ዓመት ከልምምድና ከውድድር ርቀው እንደመቆየታቸው፣ የውድድሩን ጫና መቋቋም ይከብዳቸዋል የሚል ስጋት የነበረ ቢሆንም አጀማመራቸው ከተጠበቀው በላይ መልካም የሚባል ሆኗል። ክለቦቹ በክልሉ ከነበረው ችግር አንጻር በአጭር ጊዜ በመደራጀት ለውድድር መብቃተቸው እራሱ የሚበረታታና የሚደነቅ ነው። ከእግር ኳስ ለአንድ እና ሁለት ወራት መራቅ እንኳን ዋጋ በሚያስከፍልበት በዚህ ዘመን ችግሮችን ተቋቁሞ ወደ ውድደር መመለስ ሌሎቹ ክለቦች ሊማሩበት የሚገባም ትልቅ ማሳያም ጭምር ነው። ከሁሉም በላይ እንደ አዲስ በመተግበር ላይ የሚገኘውን የክለቦች ፍቃድ አሰጣጥንም በማሟላት ለውድድሩ መብቃት እንዲሁ ለአንዳንድ ክለቦች እራሳቸውን መፈተሽ እንደሚገባ የሚያመላክትም ይሆናል።




**በ2017 ወደ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የተመለሱት ሶስቱ የትግራይ ክልል እግር ኳስ ክለቦች፣**

ለአንድ ክለብ መመዘኛነት መሠረታዊ የሚባሉትን አስገዳጅ መስፈርቶችን አሟልተው እና የክለብ ምዝገባን አከናውኖ ወደ ትልቅ ውድድር መመለስ ተጨማሪ ጉልበት እንደሚሆን እነዚህ ክለቦች ማሳያ ናቸው። አብዛኞቹ የሊጉ ክለቦች የክለብነት መስፈርትን ይዞ ባለመገኘታቸው እንደ ክለብ መወጣት የሚገባቸወን ኃላፊነት ሳይወጡ ቀርተው መነጋገርያ እስከ መሆንም ደርሰዋል። ፈተናዎች ያልበገሯቸው ክለቦቹ ግን አስፈላጊውን የሰው ኃይል እና የቢሮ አደረጃጀት አሟልተው ወደ ሊጉ ተመልሰዋል፡፡

መቐለ 70 እንደርታ፣ ውልዋሎ ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እና ስሁል ሽረ በሊጉ ጅማሬ ባካሄዷቸው ሁለት እና ሶስት ጨዋታዎች ጥሩ ተፎካካሪ መሆናቸውን አሳይተዋል። ክለቦቹ እስከ አሁን በጥቂት ጨዋታዎች ባስመዘገቡት ጥሩ ውጤት በደረጃ ሰንጠረዡም የተሻለ ቦታን መያዝ ችለዋል። መቐሌ 70 እንደርታ እና ስሁል ሽረ ጠንካራ ተፎካከሪ ሆነው የተመለሱ ሲሆን ከትልልቅ የሊጉ ክለቦች ጋር ባደረጉት ጨዋታ ነጥቦችን እየሰበሰቡም ይገኛሉ፡፡

በሊጉ መክፈቻ መርሃግብር ሃዲያ ሆሳዕናን የገጠሙት የእንደርታ ቀያይ አናብስት በጨዋታው ቢሸነፉም ጥሩ እንቅስቃሴ ማድረግ ችለው ነበር። ለዓመታት ከውድድር ርቀው እንደመቆየታቸው ከነብሮቹ ጋር ተፎካክረው 1 ለዜሮ በሆነ ጠባብ ውጤት ነበር የተሸነፉት። በሁለተኛ ሳምንት መርሃግብርም ከፕሪሚየር ሊጉ ጠንካራ ክለቦች መከካል አንዱ ከሆነው ፋሲል ከነማ ጋር ተመጣጣኝ ፉክክር አድርገው ነጥብ ተጋርተው ወጥተዋል። ከጨዋታ ወደ ጨዋታ እየተቀናጁ የመጡት መቐለ 70 እንደርታዎች በሶስተኛ ሳምንት የሊጉ መርሃግብር ፈረሰኞቹን መርታታቸው ደግሞ ያልተጠበቀ ነበር። የሊጉን ታላቅ ክለብ ቅዱስ ጊዮርጊስን 1 ለ 0 የረቱ ሲሆን በአሠልጣኝ ዳንኤል ፀሃዬ እየተመሩ ከውድድር ከመራቃቸው በፊት ወደነበሩበት ጠንካራ ተፎካካሪነት ለመመለስ ጥሩ ጅምር ላይ ይገኛሉ።

ስሁል ሽረ በተመሳሳይ ከዓመታት በኋላ ወደ ውድድሩ በተመለሰበት ዓመት ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆን በጥሩ ውጤት መጀመር ችሏል። ሁለት ጨዋታዎችን ከሊጉ ጠንካራ እና ውብ እግር ኳስን የሚጫወቱ ክለቦችን ገጥሞ አራት ነጥቦችን ከሰበሰቡት ክለቦች ተርታ ይገኛል። በመጀመርያ ሳምንት ጨዋታ አዳማ ከተማን አስተናግዶ ሶስት ለ ሁለት በመርታ ሊጉን በድል የጀመረበትን ውጤት አስመዝግቧል። በሁለተኛ ሳምንት ጨዋታቸው ሃዋሳ ከነማን አስተናግደው አንድ አቻ በመለያየት  የራስ መተማመኑን ይበልጥ ማጎልበት ችሏል። የክለቡም ድል ምንያህል በጥንካሬ ወደ ሊጉ እንደተመለሱ አመላካች ከመሆኑም በላይ የሊጉ ክለቦች የሚገኙበትን ደካማ አቋም የሚያሳይም ነው። ከሶስቱ ክለቦች እስከ አሁን ድል ያልቀናው ወልዋሎ አዲግራት ዩኒቨርሲቲ ቢሆንም መጥፎ የሚባል የሜዳ ላይ እንቅስቃሴ አላደረገም። በሁለት የሊጉ ጨዋታዎች ጥሩ ፉክክር በማድረግ በጠባብ ውጤቶች ተሸንፎ ውድድሩን በተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡

በ18 ክለቦች መካከል ተካሂዶ በውድድር ዓመቱ መጨረሻ የዋንጫ አሸናፊዎች የሚለዩበት 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ከስርጭት፣ ከደጋፊ ድርቅ እና ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ማን ዋንጫውን ያነሳል የሚለው እና ከሊጉ የትኞቹ ክለቦች ይወርዳሉ የሚለው በጉጉት ይጠበቃል፡፡


## ትግራይ ክልል

በኣቶ ሓጎስ ፍፁም የተመዝገበ የሰሌዳ ቁጥር- ጋም-01-00381 ሞተር ቁጥር- AFZWDA01099 የሻንሲ የቁጥር- MD2A25BZ5DWA45314 ሞዴል- RE-45 ትራይ ሳይክል ሰሌዳ ስለጠፋቸው ምትክ እንዲሰጣቸው 30/09/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ ሠሌዳውን ወድቆ፤ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን : ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በሽሬ-እ/ስላሰ ትራንስፖርት አገልግሎት ጽ/ቤት የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የሥራ ሂደት**

ኣቶ ዘይኑ ናስር የተመዝገበ ሰሌዳ ቁጥር- ትግ-01-00707 ሞተር ቁጥር- AFZWDC60189 የሻንሲ ቁጥር- MD2A25BZ8DWC79558 ሞዴል- RE205 ትራይ ሳይክል ሰሌዳ ስለጠፋቸው ምትክ እንዲሰጣቸው በቀን 30/09/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ ሠሌዳውን ወድቆ፤ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን : ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በሽሬ-እ/ስላሰ ትራንስፖርት አገልግሎት ጽ/ቤት የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የሥራ ሂደት**

## ድሬዳዋ አስተዳደር

የባለንብረቱ ስም ዳምጦ ድሮ ገለቱ የሰሌዳ ቁጥር 03-07148 ኢት የሻንሲው ቁጥር፡18BIF17.5*0111 ሞዴል sheshiernt 18185 ሰሌዳ ቁጥር 03-07148 ኢት ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ የኋላ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ 24/12/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ባለስልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አለምሰገድ ገ/ማሪያም/የጠቅላላ ስራ ተቋራጭ/ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-75824 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JTFDE626440109291 ሞዴል LN166L-PRMDSV የሞተር ቁጥር 3L-5363937 የሊብሬ ቁጥር 159786 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪው ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ20/1/2017 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፤ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

## የምግብ እህል እና የብጣሪ እህል ለመሸጥ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር ኢግስኮ - ኢምዘደውአዘ/ጨሽ/ 01 ሠነድ/2017

የኢትዮጵያ ምርጥ ዘርና የደን ውጤቶች አቅርቦት ዘርፍ በአርዳይታ፣በኮፈሌ እና በሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ላይ የሚገኘውን የምግብ እህል እና የብጣሪ እህል በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ስለሚፈልግ፡-

1. ማንኛውም ተጫራች በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላችሁ እና የዘመኑን የመንግስት ግብር የከፈሉ፡፡
2. ማንኛውም ተጫራች የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 2% በኢትዮጵያ ምርጥ ዘርና የደን ውጤቶች አቅርቦት ዘርፍ ስም የጨረታ ማስከበሪያ (Bid Bond) በባንክ በተረጋገጠ በCPO ብቻ ዋስትና ማስያዝ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነዱን ከላይ በተጠቀሱት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም ከአዲስ አበባ ዋናው መ/ቤት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ማንኛውም ተጫራች የተገለፀውን መጠን የምግብ እህል እና የብጣሪ እህል መጫረት ይችላል፤
5. ማንኛውም ተጫራች የምግብ እህሉ እና የብጣሪ እህሉ በሚገኙበት ቅ/ጽ/ቤቶች በመገኘት አይቶ መጫረት አለበት፡፡ ይህን ሳያደርግ ዋጋ ቢያቀርብ ኃላፊነቱ የተጫራቹ ይሆናል፡፡
6. ማንኛውም ተጫራች የዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ የሚጠይቀውን በሙሉ አሟልቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
7. ማንኛውም ተጫራች በሌላ ተጫራች ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡
8. የምግብ እህል እና የብጣሪ እህል መጠን በዚህ ጨረታ ሠነድ ላይ ከተገለፀው መጠን ሊያንስ ይችላል፡፡
9. ዋጋውን በኤንቬሎፕ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ማስገባት የሚቻል ሲሆን ጨረታው ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ በ 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ቀን ጥቅምት 05 ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ በ8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዘርፍ ጽ/ቤት አዳራሽ እና ከላይ በተጠቀሱት ቅ/ጽ/ቤቶች ጨረታው ይከፈታል፡፡
10. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስልክ ቁጥር 011 6 18 61 25 አዲስ አበባ**

**በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን**
**የኢትዮጵያ ምርጥ ዘርና የደን ውጤቶች አቅርቦት ዘርፍ**